# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 023 መስከረም 23 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# የኃይል አቅርቦት ማርሽ ቀያሪዎቹ የዓባይ ግድብ ተጨማሪ አምስት ተርባይኖች



ገጽ 4




# በአጨቃጫቂ ጉዳዮች ላይ መግባባትን ለማምጣት ሀገራዊ ምክክሩ ወሳኝ ምዕራፍ ይሆናል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- መጪው ሀገር አቀፍ ምክክር በአጨቃጫቂ ጉዳዮች ላይ መግባባትን ለማምጣት በሚደረገው የጋራ ጥረት ወሳኝ ምዕራፍ ይሆናል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለፁ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን አመራሮች ጋር የኮሚሽኑን የሥራ አፈጻጸም በተመለከተ ውይይት ያደረጉ ሲሆን የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር መስፍን አርአያ (ፕ/ር) እስከ አሁን የተከናወኑ ሥራዎችን በተመለከተ ገለጻ አድርገዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማኅበራዊ ትስስር ገፃቸው ባሰፈሩት መልዕክትም ዛሬ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን

በአጨቃጫቂ ጉዳዮች... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ለከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ሪፖርት አቅርቧል




# «አዲስ አበባ ሕፃናትን በማሳደግ የአፍሪካ ምርጥ ከተማ መባል እስክትችል ድረስ እንሠራለን»

- ከንቲባ አዳነች አቤቤ



አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- አዲስ አበባ ሕፃናትን በማሳደግ የአፍሪካ ምርጥ ከተማ መባል እስክትችል ድረስ እንሠራለን ሲሉ የከተማዋ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ገለጹ። በከተማዋ በሦስት ዓመታት ውስጥ 750 ሕፃናት ከሕፃንነት እስከ ዩኒቨርሲቲ ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል።

«አንድ ቤተሰብ፤ ለአንድ ሕፃን» በሚል መሪ ሃሳብ 100 ሕፃናትን እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ለማስተማርና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል መርሐ ግብር ትናንት ተካሂዷል።

በመርሐግብሩ ላይ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፤ አዲስ አበባን፤ ልጆች እንደ ልብ ቦርቀውባት በአእምሮና በአካል ታንጸው እንዲያድጉባት በማድረግ አፍሪካ

«አዲስ አበባ ሕፃናትን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# ኢትዮጵያ ከአውሮፓ ኅብረት ጋር የ650 ሚሊዮን ዩሮ የድጋፍ ማዕቀፍ ስምምነት ተፈራረመች

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከአውሮፓ ኅብረት ጋር ለአረንጓዴ ልማት፣ ለሰብዓዊ ልማትና

ኢትዮጵያ ከአውሮፓ.. ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ለቀጣናው ሠላም መስፈን በጋራ እንዲሠሩ የኢጋድ ዋና ጸሐፊ አስገነዘቡ

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ቀጣናዊ ትስስራቸውን በማጠናከር ለቀጣናው ሠላምና ዕድገት በጋራ ሊሠሩ እንደሚገባ የምሥራቅ አፍሪካ በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) ዋና ጸሐፊ ገለጹ። የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና የድንበር መሬት ፍኖተ ካርታ ሊዘጋጅ ነው።

18ኛው የአፍሪካ ቀንድ ኢኒሼቲቭ የሚኒስትሮች ስብሰባ ትናንት ሲካሄድ የኢጋድ ዋና ጸሐፊ ወርቅነህ ገበየሁ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ በምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ሠላምና ዕድገት ማረጋገጥ የዕለት ተዕለት ተግባር ሊሆን ይገባል።

በቀጣናው የሚገኙ ሀገራት በታሪክና በባህል የተሳሰሩ እንደመሆናቸው የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነታቸውን ማጠናከር፣ የተፈጥሮ ሀብትን በጋራ ማልማትና የድንበር ላይ ንግድን ማሳለጥ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የሚኒስትሮቹ ስብሰባ የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና የድንበር መሬቶች ጉዳይ አንዱ አጀንዳው መሆኑንም ዶክተር ወርቅነህ አንስተዋል።

የድንበር መሬት ፍኖተ ካርታ ለአካባቢ ብልጽግና፣ ለሠላም መስፈንና ለአጠቃላይ ዕድገት ወሳኝ በመሆኑ የድንበር መሬት ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ መሆኑንም ገልጸዋል።



ወርቅነህ ገበየሁ (ዶ/ር)

በቀጣናው ሀገራት የሚዘጋጀው ፍኖተ ካርታ በአፍሪካ ቀንድ ድንበሮች አካባቢ ልማትን ለማፋጠን፣ የድንበር መሬትን ለማልማት፣ የጋራ ራዕይና ስትራቴጂ ለማዘጋጀት እንደሚጠቅም ተናግረዋል። የተገለሉ ማኅበረሰቦችንም ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማስፈን የላቀ ድርሻ እንደሚኖረውም አስገንዝበዋል።

በሀገራቱ መካከል የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና የድንበር መሬት ፍኖተ ካርታ ለማዘጋጀት ቁርጠኝነቱ አለ ያሉት ዶክተር ወርቅነህ፤ ትግበራውን ዕውን ለማድረግ አሳታፊነትን መሠረት ያደረገ ሥራ ማከናወን ተገቢ ነው ብለዋል።

የድንበር ኬላን የንግድ መሸጋገሪያ፣ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት የማኅበራዊና ባህላዊ ትስስር ማጠናከሪያ፣ ፖለቲካዊ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ማዕከል ሆኖ እንዲያገለግል መሥራት ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

የግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንቶች በኢትዮጵያ ለማስፋፋት የአውሮፓ ኅብረትና አባል ሀገራት ሂደቱን በአወንታዊ እንደሚደግፉም አስታውቀዋል።

በቀጣናው የጋራ ዓለም አቀፋዊ ተግዳሮቶችን ለመፍታትና ሀገራዊ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ትኩረት ማድረጉንም ጠቁመዋል።

የፍኖተ ካርታውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ መተባበር፣ መሠረተ ልማቶችን ማሻሻል፣ ቀጣይነት ያለው ሠላም ግንባታ ማስፋፋት እንደሚገባም አመላክተዋል።

18ኛው የአፍሪካ ቀንድ ኢኒሼቲቭ ኢትዮጵያን፣ ኬንያን፣ ሶማሊያን፣ ጂቡቲን፣ ኤርትራን፣ ሱዳን እና ደቡብ ሱዳንን በአባልነት ያቀፈ ሲሆን ከየካቲት 2015 ዓ.ም ጀምሮ የአፍሪካ ቀንድ ኢኒሼቲቭን ኢትዮጵያ በሊቀመንበርነት እየመራች ትገኛለች።

# ኢሬቻ ባህላዊ እሴቱን በጠበቀ መንገድ እንዲከበር ወጣቶች ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል

ሄለን ወንድምነው



ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

አዲስ አበባ፡- የኢሬቻ በዓል ባህላዊ እሴቱን በጠበቀ መንገድ በሠላም እንዲከበር ወጣቶች ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል ሲል የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በሸገር ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮዎች አዘጋጅነት የኢሬቻ በዓል አከባባርን አስመልክቶ በሁለቱም ከተሞች ከሚገኙ ወጣቶች ጋር ትናንት ውይይት ተደርጓል።

የአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በቢሮ ኃላፊ ማዕረግ የስፖርት ትምህርት፣ ሥልጠና እና ማዘውተሪያ ስፍራዎች ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ኮሚሽነር ተስፋዬ አሜጋ በወቅቱ እንደገለጹት፤ የኢሬቻን በዓል ባህላዊ እሴቱን አስጠብቆ በሠላም እንዲከበር የወጣቶች ሚና ከፍተኛ ነው።

የኢሬቻ በዓል የሠላም፣ የፍቅር፣ የአብሮነት፣ የይቅርታና የእርቅ መገለጫ ነው ያሉት ኮሚሽነር ተስፋዬ፤ ወጣቶች ይህንን ታሳቢ በማድረግ ለበዓሉ ድምቀት ድጋፍ በማድረግ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

ወጣቶች ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገራት በዓሉን ለማክበር የሚመጡ እንግዶችን በኢትዮጵያዊ የእንግዳ አቀባበል ባህል መሠረት ተቀበለው ተገቢውን እንክብካቤ ሊያደርጉላቸው እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ኢሬቻን በርካታ ሰዎች በጋራ የሚያከብሩት በዓል ነው ያሉት ኮሚሽነር ተስፋዬ፤ ተቀያይመው የነበሩ ሰዎች ይቅርታ የሚጠያየቁበትና ከክረምት ወደ መስከረም ያሸጋገራቸውን ፈጣሪ የሚያመሰግኑበት በዓል በመሆኑ ከግጭት ይልቅ እርቅን በመስበክ ሊከበር ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

የሸገር ከተማ ምክትል ከንቲባ አቶ ጉዩ ገልገሎ በበኩላቸው፤ ኢሬቻ የዓለም ቅርስ ሆኖ በዩኔስኮ የተመዘገበ በዓል በመሆኑ በተወሰነ የማኅበረሰብ ክፍል ብቻ የሚከበር ሳይሆን ሁሉም ኢትዮጵያውያን የገዳ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ በአንድነት የሚያከብሩት ነው ብለዋል።

ወጣቶች የመስቀል ደመራና የመውሊድ በዓላትን በሠላም እንዲከበሩ ያደረጉትን አስተዋጽኦ ያደነቁት አቶ ጉዩ፤ በተመሳሳይ የኢሬቻ በዓልም በሠላም እንዲከበር ወጣቶች የድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል።

እንደ አቶ ጉዩ ገለጻ፤ የኢሬቻ በዓል የኦሮሞን ባህል ለሌሎች ለማስተዋወቅ፣ ትውፊቱን አስጠብቆ ለማኖር፣ የበዓሉን እሴት ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍና አንድነትን ለማጠናከር ከፍተኛ ሚና አለው።

በዓለም ቅርስነት የተመዘገበውን የኢሬቻን በዓል ይበልጥ ለዓለም ሕዝብ ለማስተዋወቅ ወጣቱ ጥረት ሊደረግ እንደሚገባ ገልጸዋል።

የኢሬቻ በዓል የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ለማጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ያሉት ምክትል ከንቲባው፤ ልዩነትን በማጥበብ አንዱ የአንዱን ባህል በማክበርና በመጠበቅ ሠላማዊ በሆነ መንገድ ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ እንዲከበር የወጣቱ ሚና ጉልህ ነው ብለዋል።

በዓሉ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ ከኦሮሞ ሕዝቦች ባለፈ ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች በአንድነት ሊያከብሩት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ወጣቱ በዓሉ እሴቱን ጠብቆ እንዳይከበር ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ አካላትን በጋራ መከላከልና በሕግ አካላት ተጠያቂ እንዲሆኑ ሊያደርጓቸው እንደሚገባ አሳስበዋል።

# ለአማራ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት አወንታዊ ፍላጎት ያለው ሁሉ የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ ቀረበ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ለአማራ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት አወንታዊ ፍላጎት ያለው ሁሉ ዘላቂ ሠላም እንዲሰፍን የድርሻውን እንዲወጣ የክልሉ መንግሥት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ጥሪ አቀረበ።

የአማራ ክልል መንግሥት ኮሙኒኬሽን ቢሮ በክልሉ የተፈጠረው የሠላም እጦት ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት ያስከተለ መሆኑን አስታውቋል።

በዚህ ወቅት በብዙዎቹ አካባቢዎች የተፈጠረውን አንፃራዊ ሠላም የበለጠ በማስፋትና በመጠቀም የሕዝቡን የሠላምና የልማት እንቅስቃሴ ወደ ነበረበት ለመመለስ እንደ ወትሮው ሁሉ ሠላምን የወል ሀብት በማድረግ መንቀሳቀስ እንደሚገባ ቢሮው ጥሪውን አቅርቧል።

ቀደም ሲልም ሆነ በአሁኑ ወቅት በክልሉ ያጋጠሙ ችግሮችን በሠለጠነ መንገድ ለመፍታትና ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድምና እህቶች ጋር በመተባበር ለምትገነባው ኢትዮጵያ ትልቁ ቅድመ ሁኔታ ሠላም መሆኑን ቢሮው በመግለጫው አመላክቷል።

ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች ከሠላም በተቃራኒ ግራና ቀኝ በተወጠሩ ዋልታ ረገጥ እሳቤዎች በወለዱት ግጭትና ቀውስ የሚፀና ማንነትና የሚገነባ ሀገር አለመኖሩን በአንክሮ ሊገነዘቡት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ቢሮው ጠቁሟል።

ዕውነታውን በመረዳት ሕዝቡ አሁን እንደታየው ሁሉ መላ ቀልቡን ወደ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት መመለስ አለበት ሲል ቢሮው መልዕክት አስተላልፏል።

ሕዝቡ የሃሳብ ልዩነትን በጠብመንጃ አፈሙዝ ለመፍታት እየተንቀሳቀሱ ያሉ ኃይሎችን ወደ ጎን በመተው በእጁ የገባውን አንፃራዊ ሠላም ዘላቂ እንዲሆን መሥራት ይጠቅበታል ሲል የክልሉ መንግሥት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ገልጿል።

ለዚህም ሕዝቡ የሠላም ጠባቂ ከሆኑ የፌዴራልና የክልሉ የጸጥታ ኃይሎች ጋርም ተባብሮ መሥራት ይኖርበታል ብሏል ቢሮው በመልዕክቱ።

ከዚህ ጎን ለጎን የሠላም መታጣት ችግሩ እያስተጓጎለ ያለውን የልማት ሥራ እንደገና በእልህና በወኔ በፍጥነትና በጥራት በየደረጃው ካለ የመንግሥት ሠራተኞችና ባለሙያ ጋር በመተባበር ወደ መደበኛ ሥራው ሊገባ እንደሚገባም አሳስቧል።

# «ኢሬቻ አንዱ ለሌላው ደህንነት የሚጨነቅበት የሠላምና የፍቅር በዓል ነው»

\- ሂሩት ካሳው(ዶ/ር)
የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- ኢሬቻ አንዱ ለሌላው ደህንነት የሚጨነቅበት የሠላምና የፍቅር በዓል መሆኑን የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው ተናገሩ።

የኢሬቻ ሣምንት የመክፈቻ መርሐ ግብር ከትናንት በስቲያ በአዲስ አበባ ሸራተን አዲስ ሆቴል በተካሄደበት ወቅት በመድረኩ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ባህል፤ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው፤ ኢሬቻ ፍቅር ከፍ የሚልበት ጸብና ጭቅጭቅ ቦታ አጥተው አንዱ ለሌላው ደህንነት የሚጨነቅበት የሠላምና የፍቅር በዓል መሆኑን አመላክተዋል።



በክረምቱ መውጣትና ብራ መሆን አዲስ ተስፋ የሚሰነቅበትና የተዘራውን ቡቃያ አብቦ ምድር በአረንጓዴ ስታጌጥ የኦሮሞ ሕዝብ ለፈጣሪ ምስጋና ለማቅረብ እርጥብ ሳር ይዞ ለምስጋና የሚወጣበት በዓል መሆኑን ጠቁመው፣ በዓሉ የሰው ልጆች በአንድነትና በፍቅር ተከባብረው አብረው መኖር እንዳለባቸው የሚገነቡት እሴት መሆኑን አብራርተዋል።

እንደ ዶክተር ሂሩት ገለጻ፤ በዓሉ የሠላምና የእኩልነት በመሆኑ ሕዝቦች የቋንቋና የእምነት ድንበር ሳይለያቸው በአንድነት የሚያከብሩት የሠላምና የአንድነት በዓል ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ በብዝሃ ማንነት የደመቀች በብዙ ባሕላዊ ትውፊቶችና እሴቶች ድንቅ ማንነቶች ተሸምና አምራና ደምቃ የምትታይ ውብ ሀገር መሆኗን ገልጸው፤ ባህል አንድ ማኅበረሰብ ማኅበራዊ መስተጋብሩን የሚያጠናክርበት መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢሬቻ የሰው ልጆች በሠላምና በፍቅር ተከባብረው አብረው መኖር እንዳለባቸው የሚደነግግ እሴት መሆኑን ገልጸው በዓሉ የምስጋና ቀን እንደሆነም አብራርተዋል።

ምድረ ቀደምት ኢትዮጵያ ልጆቿ በልዩነት አጊጠው በአንድ ሀገር ጥላ ስር በኅብረ ብሔራዊ ወንድማማችነትና እህትማማችነት በሠላምና በፍቅር ተሰባስበው የሚኖሩባት ሀገር ነች ያሉት ዶክተር ሂሩት ኢትዮጵያ የእምነትና የባሕል ልዩነት ሀገር ከመመስረትና ከማጽናት ያላገዳቸው ጠንካራ ሕዝቦች መኖሪያ መሆኗንም ጠቁመዋል።

አዲስ አበባ ሁላችንም በጋራ የምንኖርባት የሁላችንም ከተማና አፍሪካዊት መዲና ናት ያሉት ዶክተር ሂሩት የኢሬቻ በዓል ኢትዮጵያ በውጭው ዓለም ጎልታ እንድትታይ በማድረግ ቱሪስቶች ወደ ከተማዋ እንዲመጡ በማድረግ በቱሪዝሙ ዘርፍ ከፍተኛ ገቢ እያስገኘ መሆኑን ገልጸዋል።

የኢሬቻ ሣምንት ማስጀመሪያ መርሐ ግብሩ የኢሬቻን እሴቶች ለማስተዋወቅ ያለመ እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን፣ በመርሐ ግብሩ በዓሉን የሚያስተዋውቁ የግጥም፣ የፋሽን ትርኢትና ባህላዊ ጭፈራዎች ቀርበዋል። አባገዳዎችም በዓሉ እሴቱን ጠብቆ እንዲከበር ቄሮና ቀሬዎች የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ አስተላልፈዋል።

በማስጀመሪያ መርሐግብሩ የአዲስ አበባ ከተማ አመራሮች፣ አባገዳዎች፣ አርቲስቶች፣ የማኅበራዊ ሚዲያ አንቂዎችና ተጽዕኖ ፈጣሪዎች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

# ጉባኤው ኢትዮጵያ በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ያስመዘገበችውን ለውጥ ለዓለም ለማሳወቅ ይረዳል

ራስወርቅ ሙሉጌታ

አዲስ አበባ፡- የ2023 ዓለምአቀፉ የቴሌኮም ኅብረት (ITU) አህጉራዊ ጉባኤ ኢትዮጵያ በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ዘርፍ ያስመዘገበቻቸውን ለውጦች ለዓለም ለማሳወቅ እንደሚረዳ ተገለጸ።

ዓለምአቀፉ የቴሌኮም ኅብረት ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በጋራ ያዘጋጁት አህጉራዊ ጉባኤ «ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ለቀጣይ ዘላቂና ፍትሐዊ ዲጂታል ለውጥ የዘላቂ የልማት ግቦች ትግበራ በአፍሪካ ማፋጠን» በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት መካሄድ ተጀምሯል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሁሪያ ዓሊ በጉባኤው መክፈቻ ላይ እንደተናገሩት፤ ከ40 ሀገራት የተውጣጡ ልዑካን የታደሙበት የዓለምአቀፉ የቴሌኮም ኅብረት አህጉራዊ ጉባኤ በዘርፉ እየተከናወኑ የሚገኙ ሥራዎችን ለዓለም በማሳየት ኢትዮጵያ በሌሎች ሀገራት የሚኖራትን ተቀባይነት ለማሳደግ ይረዳል።

ከዚህ ቀደም ከ170 ሀገራት የተሰባሰቡበትና ሦስት ሺህ የሚደርሱ ተሳታፊዎች የታደሙበት 17ኛው የኢንተርኔት ገቨርናንስ ጉባኤ በኢትዮጵያ መካሄዱን ያስታወሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ መድረኩ በውጤታማነት በመጠናቀቁ እስካሁን በአሜሪካና በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ሲካሄድ የነበረውን የዓለምአቀፉ የቴሌኮም ኅብረት አህጉራዊ ጉባኤ በኢትዮጵያ እንዲዘጋጅ ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

ተመሳሳይ ጉባኤዎች በሀገሪቱ ስላለው የዘርፉ ተጨባጭ ለውጥ ለቀሪው ዓለም ተደራሽ ለማድረግ እንደሚጠቅሙ አስረድተዋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ እንዳመለከቱት፤ በዓለም ያለው እንቅስቃሴ ወደ ዲጂታል ቴክኖሎጂ እየተቀየረ ይገኛል። ይህንን እንደሀገር እውን በማድረግ ኢትዮጵያ ቀሪው ዓለም ጋር እንድትጓዝ ለማድረግ የ2025 የዲጂታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂ ተቀርጾ እየተተገበረ ይገኛል።

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ አብዛኛው አገልግሎት ወደዲጂታል አሠራር እንዲቀየር በግል ተቋማትም ሆነ በመንግሥት በኩል እየተሠራ ይገኛል ያሉት ወይዘሮ ሁሪያ፤ መሠረተ ልማቶችን በማሟላትና የዲጂታል አስቻይ ሥርዓቶች እንዲኖሩ ጥረት እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

መንግሥት ዘርፉን የሚደግፉ ፖሊሲዎች በማዘጋጀት ወደሥራ በመግባት ላይ መሆኑን ጠቁመው፤ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ መውጣቱ፣ የቴሌኮም ዘርፍን ከመንግሥት ነፃ በማድረግ ተወዳዳሪዎች እንዲገቡ መደረጉ፣ ብሔራዊ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት መጀመሩ፤ የዲጂታል ክፍያ ሥነ-ምህዳርን የማዳበር፤ የኢ-ኮሜርስና ሌሎች ዲጂታል አገልግሎቶችን የማሳደግ እንዲሁም የሳይበር ጥቃትን የመከላከል አቅምን የማጎልበት ሥራዎች ከፍተኛ ለውጥ የተመዘገበባቸው መሆናቸውን አስታውቀዋል።

በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ 69 ሚሊዮን ዜጎች የሞባይል ስልክ ተጠቃሚ መሆናቸውን እንዲሁም ከ23 ሚሊዮን በላይ የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች መኖራቸውን ገልጸው፤ እንደሀገር የተጠቃሚ ቁጥርና የአገልግሎት ጥራት የማሳደግ፣ እንዲሁም ተመጣጣኝ የአገልግሎት ዋጋ የመፍጠርና የቋንቋ ተደራሽነትን ማጎልበት እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

የ2023 ዓለም አቀፉ የቴሌኮም ኅብረት (ITU) አህጉራዊ ጉባኤ ለአፍሪካ ቀጣይነት ያለውና ፍትሐዊ ዲጂታል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል ሲሉ ተናግረዋል።

እስካሁን የኢንተርኔት አገልግሎት የሚያገኙ አፍሪካውያን 43 በመቶ ብቻ ናቸው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በአንጻሩ በአህጉሪቱ በፍጥነት እያደገ ያለውን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት እየተከተሉ ሁሉም ሰው በዲጂታል ኢኮኖሚ ውስጥ የመሳተፍ ዕድል እንዲኖረው በመሠረተ ልማትና በክህሎት ልማት ላይ ኢንቨስት ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

ጉባኤው የአፍሪካ አህጉር ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ለማፋጠንና የዘላቂ ልማት ግቦችን በማሳካት ረገድ በጋራ ለመሥራት በር የሚከፍት መሆኑን ገልጸዋል።

መድረኩ በዓለም አቀፉ የቴሌ ኮሙኒኬሽን ማኅበርና በኢኖቬሽን ቴክኖሎጂና ሚኒስቴር በጋራ የተዘጋጀ ሲሆን «ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ለቀጣይ ዘላቂና ፍትሐዊ ዲጂታል ለውጥ የዘላቂ የልማት ግቦች ትግበራ በአፍሪካ ማፋጠን» በሚል መሪ ቃል ከመስከረም 22 እስከ 24 ቀን 2016 ዓ.ም እየተካሄደ ይገኛል።

# ኢሬቻ የሠላምና የወንድማማችነት ዓርማ ነው

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- ኢሬቻ የሠላምና የወንድማማችነት ዓርማ ነው ሲሉ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የማኅበራዊ ክላስተር አስተባባሪው አቶ አብዱልሀኪም ሙሉ ገለጹ። የኢሬቻ በዓልን በማስመልከት የተዘጋጀው የኢሬቻ አውደርዕይና ባዛር ትናንት በኦሮሚያ ባህል ማዕከል ተከፍቷል።

በወቅቱ በኦሮሚያ ክልል በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የማኅበራዊ ክላስተር አስተባባሪ አቶ አብዱልሀኪም ሙሉ፤ ኢሬቻ የሠላም የአንድነትና የወንድማማችነት ዓርማ መሆኑን ጠቁመው፤ የበዓሉ አክባሪ የሆነ ሁሉ ባህሉን ሳይዘነጋ የሌላውን ባህል በማክበር ኢትዮጵያዊነትን በሚያጎላ መልኩ ሊያከብር ይገባል ብለዋል።

ለበዓሉ የተለያዩ ዝግጅቶች መደረጋቸውን የገለጹት አቶ አብዱልሀኪም፤ ከዚህ ቀደም የኦሮሚያ ቱሪዝም ሳምንት ጋር ተያይዞ ለቱሪዝሙ ዕድገት የሚረዳ ሰፊ ሥራ ሲከናወን መቆየቱን አንስተዋል።

ትውልዱን የእራሱን ባህል እንዲጠብቅና እሴቶቹን ይበልጥ እንዲያስተዋውቅ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀው የኢሬቻ አውደርዕይና ባዛር የኦሮሞን አልባሳትና ቁሳቁሶች በማሳየት ትውልዱ ባህሉን እንዲያውቅ የሚረዳ መሆኑን ተናግረዋል።

ባዛርና ኤግዚቢሽኑ አያቶቻችን ሲጠቀሙባቸው የነበሩ ማራኪና አስደናቂ የሆኑ መመገቢያዎች፣ ባህላዊ ቁሳቁሶች እንዲሁም በጀግንነት ወቅት የሚገለገሉባቸውን የተለያዩ መሣሪያዎች ለማየት ዕድል የፈጠረ መሆኑን አቶ



ፎቶ: ገበበ ገብሬ

አብዱልሀኪም ገልጸዋል።

የባዛርና ኤግዚቢሽኑ ባህልን ከፍ በማድረግ ኢትዮጵያዊነትን ያጸና ታሪክን ለትውልዱ ማሳወቅ ላይ ያተኮረ መሆኑን አቶ አብዱልሀኪም ተናግረዋል።

የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ ሁሴን በሪሶ በበኩላቸው፤ የኢሬቻ በዓል በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት እንደሚከበር ገልጸዋል።

በበዓሉ የምንታደም ሁሉ ዓርማችን የሠላምና የአባገዳ ብቻ መሆን አለበት ያሉት አቶ ሁሴን፤ በበዓሉ ላይ የየትኛውንም ፖለቲካዊ ሃሳብ የሚያንፀባርቅ ሰንደቅ ዓላማ መያዝ እንደማያስፈልግም መልዕክት አስተላልፈዋል።

# የኃይል አቅርቦት ማርሽ ቀያሪዎቹ የዓባይ ግድብ ተጨማሪ አምስት ተርባይኖች

**ተስፋ ፈሩ**

2016፤ የዓባይ ግድብ ግንባታ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ መድረሱ የተረጋገጠበት ዓመት ነው። ከብዙ ጫና በኋላ የግድቡ አራተኛ ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት የተጠናቀቀበት ከመሆኑም ባሻገር ተጨማሪ አምስት ተርባይኖች የሚገጠሙበት አመትም በመሆኑ ትልቅ ትርጉም የሚሰጠው ነው። ለመሆኑ ግድቡ አሁን የደረሰበት ደረጃና ዘንድሮ የሚተከሉት አምስት ተርባይኖች በሀገራችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊም ሆነ ፖለቲካዊ እድገት አንጻር ምን ትርጉም ይኖራቸዋል?

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኃይድሮ ፖለቲክስ ተመራማሪና የሕዳሴ ግድብ የኢትዮጵያ ተደራዳሪ ቡድን አባል ዶ/ር ያዕቆብ አርሳኖ ከዚህ ቀደም በዓባይ ግድብ ላይ ሁለት ተርባይኖች ተተክለው ኃይል ማመንጨት በመጀመራቸው በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ስርጭት ውስጥ ተጨማሪ ብርሃን እንዲሁም አዲስ የሥራና ዕድገት መሠረት መፈጠሩን ያወሳሉ። አራተኛውን ሙሌት ተከትሎ ደግሞ በጀመርነው አመት በጋ ላይ እየተገጠሙ የሚገኙት አምስት ተርባይኖች ተጠናቀው ተጨማሪ ኃይል ያስገኛሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ የገለጹት ዶ/ር ያዕቆብ፣ የሚገኘው ተጨማሪ ኃይል በከተሞች እና በኢትዮጵያ ገጠራማ አካባቢዎች የብርሃን ስርጭትን ከፍ ያደርጋሉ። በኤሌክትሪክ ኃይል አማካኝነት የሚሠሩ በርካታ የሆኑ የኢንዱስትሪና አግሮ ኢንዱስትሪ ሥራዎች እንዲስፋፉ በማድረግም ለወጣቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር ድህነትን ለመቀነስ ያግዛል ብለው እንደሚያምኑ ይገልጻሉ።

ከአምስቱ ተርባይኖች የሚመነጨው ኃይል ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገራት በሽያጭ የምታቀርበው የኤሌክትሪክ ኃይል መጠን ከፍ እንዲል በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን እንደሚያሳድግም ዶክተር ያዕቆብ ያስረዳሉ፣ «ለጎረቤት ሀገሮች ጅቡቲና ሱዳን የኃይል ሽያጭ እየተካሄደ መሆኑ የሚታወቅ ነው። ግድቡ ኃይል የማመንጨት አቅሙ እየጨመረ ሲሄድ ለጅቡቲና ሱዳን ተጨማሪ ኃይል ማቅረብ እንችላለን። በተጨማሪም ወደ ኬንያም የኃይል ተሸካሚ መስመር ዝርጋታው በመጠናቀቁ ወደፊት በርካታ ኃይል ለመግዛት ውለታ አላቸው። ከኬንያ ባለፈ ሶማሊያና ደቡብ ሱዳንን የመሰሉ ሀገራትም ለኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ጥያቄ ማቅረባቸው የታወቀ ነው። ስለዚህ ባጠቃላይ ከግድቡ የሚገኘው የኤሌክትሪክ ኃይል የሀገሪቱን ኢኮኖሚና የሥራ እንቅስቃሴ ከፍ የማድረጉን ያህል ለጎረቤት ሀገሮች እየተሸጠ የውጭ ምንዛሬ ማግኛ አንድ መንገድ የመሆኑ ዕድል ከፍ እያለ ይመጣል» ብለዋል።

አያይዘውም ኢትዮጵያ ተጨማሪ የኤሌክትሪክ ኃይል ስታመነጭ ውሃ የሚቀበሉትም ሆኑ ሌሎች ጎረቤት ሀገሮች ከኢትዮጵያ ኃይል የመግዛት ዕድላቸው ከፍ እንደሚል መዘንጋት እንደሌለበት በመግለጽ፣ ትስስሩ በኢኮኖሚ መያያዝን ከፍ ስለሚያደርግ ፖለቲካዊ ትብብር እና መቀራረብ እንዲኖር እንዲሁም ሠላምና የጋራ ብልጽግናም ለወደፊት ተስፋ ያለው ነገር እንዲሆን እንደሚያደርግ ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የውሃ ሀብት ተመራማሪውና በዓባይ ግድብ ጉዳይ ላይ አስተያየት በመስጠት የሚታወቁት ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ በበኩላቸው አምስት ተርባይን ማለት ከግድቡ አጠቃላይ ኃይል የማመንጨት አቅም አንድ ሦስተኛ ያህል መሆኑን በመግለጽ፣ ኢትዮጵያ ላላት የኤሌክትክ ኃይል አቅርቦት ትልቅ ጭማሪ ነው ይላሉ። በሥርዓት ለአገልግሎት ከቀረበ ብዙ የኃይል እጥረት የገጠማቸው ማምረቻ ድርጅቶች ተጨማሪ ኃይል እንዲያገኙ ያደርጋል። በኅብረተሰቡም ደረጃ በየቤቱ የሚደርሰው የኃይል መጠን የተሻለ ይሆናል ብለዋል።

ዶ/ር ያዕቆብም የአምስቱ ተርባይኖች ኃይል ማመንጨት መጀመር በታችኞቹ የተፋሰሱ ሀገራት የተለየ እንድምታ አይኖረውም ይላሉ። ኢትዮጵያ ገና ግድቡ ሲጀመር ጀምሮ በዓባይ ወንዝ ላይ ግድብ የመገደብ መብት እንዳላት አሳውቃለች። ፍትሐዊ የውሃ አጠቃቀም መኖር አለበት የሚል አቋም ይዛ በጥናቱ፣ በዲዛይኑ እና አሠራሩ ውሃ ተቀባይ ሀገሮች የከፋ ጉዳት ላይ እንዳይወድቁ በከፍተኛ ጥንቃቄ መነሳቷ ይታወቃል። ስለዚህ እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያ የምትደራደረው የውሃ መብቷን ለማስከበር ሳይሆን የውሃ ሀብቷን በሉዓላዊነቷ ላይ ተመስርታ የማልማት መብቷ የተረጋገጠ መሆኑን በሚገባ ለማሳየትና የታችኞቹ ተፋሰስ ሀገራት የከፋ ጉዳት እንዳይደርስባቸው በምክክር እንዲሠሩ ለማስቻል ነው ብለዋል።

በአንጻሩ ከኢትዮጵያ ውሃ የሚቀበሉ ሀገሮች በተለይም ግብጽ ኢትዮጵያ የውሃ ልማቷን እነሱን እያስፈቀደች እንድትሠራ ይፈልጋሉ ሲሉም ይወቅሳሉ።

አክለውም «ይሄ እንደማይሆን ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ እየተነገራቸው ነው። ከዚህ ቀደምም ሆነ ሁልጊዜም ቢሆን የኢትዮጵያ ሃሳብ የውሃ ልማትን እነሱን አስፈቅዶ የመሥራት አይደለም። ኢትዮጵያ ለትብብር ዝግጁ እንደነበረች ባለፉት በርካታ አስርት አመታት የተገለጸ ነገር ነው። በዓባይ ግድብም የተገለጸውና በተግባርም እየዋለ ያለው መርህ ይሄ ነው» በማለት በዚህ መሠረት እስካሁን ያለው ሥራ በሚገባ እየተሰራና የኢትዮጵያ ሀሳብ በግልጽ ለግብጽና ሱዳን እየተነገረ መሆኑን ያስረዳሉ። ወደፊት ድርድሩ የሚቀጥለው ግብጾች አስገድደን እናስፈርም በሚሉት አቅጣጫ ሳይሆን፣ ኢትዮጵያ ውሃዋን ስታለማ ግብጽና ሱዳን በከፋ ሁኔታ እንደማይጎዱ ማረጋገጫ በመስጠት የጋራ ልማት እንዲቀጥል በሚያስችል መልኩ ይሆናል ብለው እንደሚያምኑም ይገልጻሉ።

ኢትዮጵያ ግድቧን እንዳትሞላ የሚከለክላት ምንም ዓይነት ሕግም ሆነ የሞራል ገደብ አይኖርም የሚሉት ፕሮፌሰር አድማሱ፤ አምስቱ ተርባይኖች ኃይል ማመንጨት ሲጀምሩ ከታችኛው ሀገራት በኩል ጩኸት ሊበረክት እንደሚችል በመግለጽ፣ ጩኸቱን እና ፍሬ ነገሩን መለየት ያስፈልጋል በማለት ያሳስባሉ።

ፕሮፌሰር አድማሱ እንደሚናገሩት፣ የኃይል ፍላጎታችን እያደገ ሲሄድና የገቢ ምንጭም እናድርገው ስንል የዓባይ ግድብን ጨምሮ ያሉን ኃይል ማመንጫዎች ላይበቁ ይችላሉ። አሁን እያገባደድን የምንገኘውን ግድብ መያዣ አድርገው የማዋከብና የማደናገር ተግባር ላይ የሚሰማሩት የወደፊት ዕጣፈንታችን ከሆነው ሀብት የመጠቀም መብታችንን የሚገደብ ስምምነት ውስጥ እንድንገባ በመፈለግ ነው። ይህን ልናደርግ አንችልም፤ ኢትዮጵያም የምትጠነቀቀው ለዚሁ ነው። የዓባይ ግድብን የውሃ ሙሌት ምክንያት በማድረግ ወደፊት በሚገነቡ ሌሎች ግድቦች ላይ ውሳኔ ማሳለፍ ጥንቃቄ ማድረግ እንዲሁም በቂ ውይይት ይፈልጋል።

ይህ ግድብ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ የምትገነባው የመጨረሻ ግድቧ እንዳልሆነ ሊታወቅ እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥተው የተናገሩት ፕሮፌሰሩ፣ «የዓባይ ግድብ የመጨረሻዋ ነው ብሎ የሚያስብ ካለ ይሄ ምክንያታዊ አስተሳሰብ አይደለም። በኢትዮጵያ በኩል እጃችን ላይ ያለው አጀንዳ ግድቡን መሙላትና ጥቅም ላይ ማዋል ነው። በዚህ ሂደትም ኢትዮጵያ የምታባክነው ውሃ እና እነሱ የሚጎዱበት ሂደት የለም» ብለዋል።

በዓባይ ወንዝ ተጠቃሚ መሆንን በተናጠል ከመወጠን በመውጣት በጋራ እያሰብን የጋራ ፕሮጀክቶችን ጭምር አብረን መሥራት ብንለማመድ፣ ከውሃው ውጪ በባህልና ኢኮኖሚም የሚወራረስ ነገር ስላለን ብዙ ተጠቃሚ እንሆናለን ሲሉ ይመክራሉ።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) በቅርቡ እንደገለጹት፣ ዘንድሮ ወደ ሥራ ከሚገቡት አምስቱ ተርባይኖች የሚገኘው የኃይል መጠን ግልገል ጊቤ ሦስት ከሚያመነጨው የሚበልጥ እና የበለስ፣ የግልገል ጊቤ አንድና ሁለት እንዲሁም የተከዜ የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ከሚሰጧቸው አማካይ አንድ ሺህ 180 ሜጋ ዋት ተመጣጣኝ ወይም የሚበልጥ ይሆናል። ይህም ግድቡ ሳይጠናቀቅ በኢትዮጵያ ትልቁ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ እንዲሆን ያደርገዋል። በግድቡ የሚገጠሙት ተርባይኖች እያንዳንዳቸው በአማካይ ከ375 በላይ ሜጋ ዋት ኃይልን ያመነጫሉ ተብሎ ይጠበቃል።

## በአጨቃጫቂ ጉዳዮች ላይ መግባባትን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አባላትን አግኝቼ ሥራዎቻቸው ስላሉበት ደረጃ ተወያይተናል ብለዋል።

በዚህም መጪው ሀገር አቀፍ ምክክር በአጨቃጫቂ ጉዳዮች ላይ መግባባትን ለማምጣት የምናደርገው የጋራ ጥረት ወሳኝ ምዕራፍ እንደሚሆን አምናለሁ ሲሉ ገልጸዋል።

የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንትና የዋና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አደም ፋራህ በበኩላቸው፤ ፓርቲው ሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥልና በምክክሩም ንቁ ተሳታፊ ለመሆን ዝግጅት ማድረጉን ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ የተሳካ ሀገራዊ ምክክር ለማካሄድ እስካሁን ያከናወናቸው ሥራዎች የሚበረታቱ መሆናቸውን አንስተው በተለይም ምክክሩን አካታችና ሁሉን አሳታፊ ለማድረግ የሁሉንም አካላት ተሳትፎ ለማረጋገጥ የተሄደበት ርቀትና አጠቃላይ ጥረቶች የሚደነቁ መሆናቸውን አመልክተዋል።

በቀጣይም «ከማን ምን ይጠበቃል» የሚለውን በመለየትና ቀሪ ሥራዎችን በተሳካ መልኩ ለማከናወን ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየተወያየ መሆኑን ከገለጻው ለመረዳት መቻላቸውን ተናግረዋል።

ሀገራዊ ምክክሩ በዋና ዋና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት ለመፍጠር ያስችላል፤ ይህም በኢትዮጵያ ዘላቂ ሠላምን በማስፈን የብልጽግና ጉዞዋን ለማፋጠን እንደሚያስችል ጠቁመው፣ ከዚህ አኳያ ከብልጽግና ፓርቲ አባላት ጋር በተካሄደ ሰፊ ውይይት የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል ብለዋል። የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ በበኩላቸው፤ ኮሚሽኑ እስካሁን ባለው ሂደት አሳታፊ ሀገራዊ ምክክር ለማካሄድ የሚያስችሉ የዝግጅት ተግባራትን ሲያከናወን መቆየቱን ገልጸዋል።

በዚህም ኮሚሽኑ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ውይይት ማድረጉን ጠቅሰው፤ ከመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ጋር የተደረገው ውይይት ዓላማ መንግሥት ኮሚሽኑ እስካሁን ያከናወናቸውን ተግባራት ተገንዝቦ ለቀጣይ ሥራዎች የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣ ለማስቻል መሆኑን አስገንዝበዋል።

በመድረኩ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በተጨማሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት እንዲሁም ሌሎች ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

## «አዲስ አበባ ሕፃናትን በማሳደግ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከመዲናዋ መማር የምትችልበት ፕሮግራም መጀመሩን ገልጸዋል። አዲስ አበባ ሕፃናትን በማሳደግ የአፍሪካ ምርጥ ከተማ መባል እስክትችል ድረስ እንሠራለንም ብለዋል።

መንግሥት ከለውጡ ወዲህ የሚከተለው ፖሊሲ ሰው ተኮር ነው ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ ለሰው ትኩረት መስጠት እንደሚገባ በማሰብ የሚሠራው ሥራ ሁሉ የሰውን ሕይወት ምን ያህል ይቀይራል የሚል መመዘኛዎች እንዳሉት አመላክተዋል። በተለይም ተደራሽነትን ያላገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች ማኅበራዊ ፍትህን እንዲያገኙ ማድረግ ትልቁ ሥራችን ነው ብለዋል።

ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ወላጆቻቸው ምንም ገቢ ለሌላቸውና ገቢያቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት ልጆቻቸውን በትክክል ለማሳደግና ለማስተማር የምግብ፣ የቁሳቁስ፣ የጤና፣ የትምህርት ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት አቅም የሚያንሳቸውን በመለየት ድጋፍ እንዲያገኙ መደረጉን አንስተዋል።

በሦስት ዓመታት ውስጥ 750 ሕፃናትን የምግብ፣ የአልባሳት እና የትምህርት ቁሳቁስ ከሕፃንነት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ ድጋፍ እንዲያገኙ መደረጉን በመጥቀስ፤ ለዚህም የተለያዩ ተቋማትና ግለሰቦች ትብብር ማድረጋቸውን ጠቁመዋል። በመዲናዋ ለትውልድ ግንባታ በመንግሥት የተያዘው መርሐ ግብር በልዩ ትኩረት እየተሠራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ገልጸዋል።

እናት ልጇ በአእምሮና በአካል ብቁ ሆኖ ማደግ የሚችልበት ነገር ማየቷ አስደሳች ሁኔታ መሆኑን የገለጹት ከንቲባዋ፤ አዲስ አበባ ሕፃናትን በማሳደግ የአፍሪካ ምርጥ ከተማ መባል እስክትችል ድረስ እንሠራለን ነው ያሉት። ለዚህም ባለሀብቶችንና የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን በማስተባበር ሕፃናትን ተደራሽ የማድረግ ተግባር በሰፊው እየተከናወነ እንዳለ ጠቁመዋል። ከንቲባ አዳነች፤ «ትውልድን ካልገነባን ዛሬ ያልዘራነውን ነገ ማጨድ አንችልም። ዛሬ መልካም ፍሬ ከዘራን መልካም ፍሬ እናጭዳለን። ስለዚህ ትውልድን እንገነባለን። ሕፃናትን ከጽንስ ጀምረን እስከ ስድስት ወራቸው ድረስ በልዩ ፕሮግራም እናግዛለን። በትምህርት ቤት ምገባ መርሐ ግብር ሂደት ውስጥም ተጠቃሚ እንዲሆኑ እያደረግን ነው። ትውልድ ላይ ኢንቨስት ማድረግ ሀገርን ይገነባል። ትውልድን ለመገንባት ደግሞ የአንድ ሰው አሊያም የመንግሥት ብቻ ኃላፊነት አይደለም። ወላጆችን፣ ማኅበረሰቡንና፣ ባለሀብቱን ጨምሮ የሁሉም ርብርብ ሊኖርበት ይገባል» ሲሉ ተናግረዋል።

ዝቅተኛና ምንም ገቢ ከሌላቸው ቤተሰብ ለተወለዱ ሕፃናት ዘላቂ ድጋፍ መስጫ ሥነ ሥርዓት ትናንት በከንቲባ ጽሕፈት ቤት የተካሄደ ሲሆን፤ አቶ ማናዬ ሰንደቁ የተባሉ ባለሀብት ብቻቸውን ለ100 ሕፃናት ከአንድ ዓመት ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ የሚያስፈልጋቸውን ወጪ ለመሸፈን ተፈራርመዋል።

## ኢትዮጵያ ከአውሮፓ ኅብረት ጋር የ650 ሚሊዮን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለመልካም አስተዳደርና ለሠላም ግንባታ የሚውል የ650 ሚሊዮን ዩሮ የድጋፍ ማዕቀፍ ስምምነት ተፈራረመች። በኢትዮጵያ መንግሥትና በአውሮፓ ኅብረት መካከል ያለው የዲፕሎማሲ ግንኙነት በከፍተኛ ደረጃ ተሻሽሏል።

የድጋፍ ማዕቀፉን የገንዘብ ሚኒስትር አቶ አህመድ ሽዴ እና የአውሮፓ ኅብረት የዓለምአቀፍ ትብብር ኮሚሽነር ጁታ ኡርፒላይነን ተፈራርመዋል።

በወቅቱ አቶ አህመድ ሽዴ፤ በኢትዮጵያና በአውሮፓ ኅብረት መካከል ለቀጣይ አራት አመት የሚቆይ የ650 ሚሊዮን ዩሮ የባለ ብዙ ዘርፍ ዓመታዊ የድጋፍ መርሐ- ግብርም ትብብር ማዕቀፍ ስምምነት መፈጸሙን ገልጸዋል።

ስምምነቱ ባለፉት ሁለት ዓመታት ተቀዛቅዞ የነበረውን የአውሮፓ ኅብረትና የኢትዮጵያን ግንኙነት እንዲመለስ ያደርገዋል፤ ያለንን የልማትና የገንዘብ ትብብር በተወሰነ ደረጃ ያሳድገዋል ብለዋል።

የ650 ሚሊዮን ዩሮ ድጋፉ በሦስት ማዕቀፎች ላይ ያተኮረ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በኢትዮጵያ መንግሥት የሚካሄዱ የአረንጓዴ ልማት በተለይም ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተገናኙ ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ፣ የሰብዓዊ ልማት በዋናነት ሴፍቲኔት፣ የትምህርትና የጤና ፕሮጀክቶችን ለማገዝ እንዲሁም ከመልካም አስተዳደርና ከሠላም ግንባታ ጋር ለተገናኙ ጉዳዮች የሚውል መሆኑን አንስተዋል።

ሦስቱም የትብብር ማዕቀፎች በሀገሪቷ የ10 አመት የዕድገት መርሐ- ግብር ውስጥ የተካተቱ በመሆናቸው ስምምነቱ ትልቅ ትርጉም አለው ያሉት አቶ አህመድ፤ ድጋፉ ሁለተኛውን የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ለማገዝ ያለው ፋይዳ የጎላ መሆኑን አመላክተዋል።

የትብብር ማዕቀፉ በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ሳይደረግ ለተወሰነ ጊዜ የቆየበት ሁኔታ እንደነበር ያስታወሱት አቶ አህመድ፤ የአውሮፓ ኅብረት ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ አንዳንድ መሠረታዊ የልማት መርሐ ግብሮችን ሲደግፍ እንደነበር አንስተዋል።

በቀጣይ በአራት ዓመታት የትብብር ማዕቀፉን በማሳደግ በተሻለ የገንዘብ መጠን እንዲያግዙን የስምምነት ሰነዱ መፈረሙን ጠቁመዋል።

አሁን ላይ ከአውሮፓ ኅብረት ጋር ያለን የትብብር ማዕቀፍ ወደ መደበኛው የትብብር ማዕቀፍ ተመልሷል ብለዋል።

ይህም በአውሮፓ ኅብረትና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ያለው የዲፕሎማሲ ግንኙነት በከፍተኛ ደረጃ መሻሻሉን ያሳያል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ስምምነቱ ኢትዮጵያ የሠላም ግንባታዎችን በማጠናከርና የኢኮኖሚ ለውጦችን የበለጠ በማጎልበት ከልማት አጋሮች ጋር ያላትን ትብብር እያጠናከረ መሆኑንና ወደ መደበኛው መመለሱን ያሳያል።

በአውሮፓ ኅብረት የዓለምአቀፍ የአጋርነት ኮሚሽነር ጁታ ኡርፒላይነን በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ከፕሪቶሪያ የሠላም ስምምነት በኋላ ወደ ሠላምና መልሶ ግንባታ መመለሷን አንስተዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት የገጠመውን ችግር እንረዳለን ያሉት ኮሚሽነሯ፤ እንደ አጋር የአውሮፓ ኅብረት ለአራት አመት የሚቆይ የድጋፍ ስምምነት አድርገናል ብለዋል።

የአውሮፓ ኅብረት ከዚህ በፊት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያደርገውን የገንዘብ ድጋፍ አለማቆሙን ጠቁመው፤ የአሁኑ ድጋፍ የአውሮፓ ኅብረት ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ትብብር ለማጠናከር ያለውን ቁርጠኝነት እንደሚያሳይ አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያና የአውሮፓ ኅብረት በሂደት ወደ መደበኛው ግንኙነት እየተመለሱ ነው ያሉት ኮሚሽነሯ፤ የባለ ብዙ ዘርፍ የትብብር ማዕቀፍ ድጋፍ ግንኙነቱ የመደበኛነት ስለመመለሱ ማሳያ ነው ብለዋል።

ድጋፉ ለአየር ንብረት ለውጥ ሥራዎች፣ ለብዝሃ ሕይወት ጥበቃ፣ ለአረንጓዴ ልማት፣ አካባቢ ጥበቃና ታዳሽ ኃይል ልማት፣ ለሰው ኃይል ልማት እንደሚውል ገልጸዋል።

በተጨማሪም ለሠላም አስተዳደር፣ ሠላም ግንባታና የዴሞክራሲ ልማት ሥራዎች መጠናከር ድጋፉ እንደሚረዳ አስታውቀዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ ያሏትን የተፈጥሮ ሃብቶች በመረዳት እና ጥቅም ላይ በማዋል ለትውልድ የሚተርፍ ሥራ መሥራት ይገባል!

ኢትዮጵያ የበርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶች ባለቤት ነች፡፡ የተፈጥሮ ሃብቶቹ ከኤርታኢሌ እስከ ዳሎል፣ ከራስ ዳሽን እስከ ታችኛው ኦሞ ሸለቆ ድረስ የተዘረጉ ናቸው። ከእነዚህም መካከል አስደናቂ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የአየር ንብረት፣ ብርቅዬ የዱር እንስሳት፣ እንዲሁም የሰው ዘር መገኛ ስፍራዎች ተካተውበታል።

እነዚህ ደግሞ ኢትዮጵያን ለቱሪስት መዳረሻነት ከሚያበቋት ነገሮች መካከል ቀዳሚዎቹ ናቸው። ኢትዮጵያ በዓለም ቅርስነት 13 ቅርሶችን በማስመዝገብ ከአፍሪካ ቀዳሚ አገር የነበረች ሲሆን ሰሞኑን ደግሞ የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክንና የጌዲዮ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ መልክዓ ምድር፣ በማስመዘገብ በዩኒስኮ የተመዘገቡ የቱሪስት መስህቦችን 15 በማድረስ በአፍሪካ ቀዳሚነቷን ማረጋገጥ ችላለች፡፡

በተለይም ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻ ግንባታዎች በስፋት በመከናወን ላይ ናቸው፡፡ ሀገራዊ ለውጡ ዕውን ከሆነበት 2010 ጀምሮ የተፈጥሮ ሃብቶችን በማወቅ፤ በመለየት፤ በማልማትና በመጠቀም ረገድ እመርታዊ ለውጦች ታይተዋል፡፡ በአጠቃላይ ወቅቱ ለቱሪዝም ዘርፉ ትንሳኤ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

በተለይም በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሀሳብ አፍላቂነት እና መሪነት ለዘርፉ የተሰጠው ልዩ ትኩረት የሚያበረታታ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገበታ ለሸገር፤ ገበታ ለሀገር እና ገበታ ለትውልድ በሚል ማዕቀፍ በሀገራችን የሚገኙትን የቱሪዝም መዳረሻዎች በዘመናዊ መልክ እንዲለሙ እና ለቀረው ዓለም እንዲተዋወቁ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ተቀርፀው ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ መዲናችን አዲስ አበባን ጨምሮ በአራቱም ማዕዘናት ሃብቶችን በመለየትና በማልማት የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ እጅግ በርካታ ሥራዎች ተከውነዋል፡፡

በገበታ ለሸገር የቱሪስት መዳረሻዎች ግንባታ የአንድነት፤ የወንድማማች እና የእንጦጦ ፓርኮች ለአዲስ አበባ ድምቀት ሆነዋታል፡፡ ለወትሮው በቱሪስት መተላለፊያነት የምትታወቀው አዲስ አበባ የቱሪስቶች መቆያ የመሆን ዕድልም አግኝታለች፡፡ በገበታ ለሀገር ፕሮጀክትም የጎርጎራ፤ የኮይሻ እና የወንጪ የቱሪስት መዳረሻዎች ለኢትዮጵያ የቱሪዝም ዕድገት ተጨማሪ ዕድሎችን ፈጥረዋል፡፡

ሰሞኑን ደግሞ በደቡብ ምዕራብ ክልል ቤንች ሸኮ ዞን የ‹‹ገበታ ለትውልድ›› ውጥን አካል የሆነውን 'የደንቢ ሐይቅ ሎጅ' የመሰረተ ድንጋይ የማስቀመጥ ተግባር ተከናውኗል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን የጅማ ከተማ በአዲሱ ገበታ ለትውልድ ከተመረጡ ቦታዎች ውስጥ አንዷ ሆናለች፡፡ የጅማ ገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት የከተማውን ገጽታና የአኗኗር ዘይቤ በእጅጉ እንደሚለወጥም ታምኖበታል።

ሚዛን አማን ላይ የሚሠራው አዲስ ሪዞርትና ኮይሻ አካባቢ የሚሠራው ፕሮጀክት ከጅማ ከተማ በቅርብ ርቀት የሚገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ቦታዎች የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶችን ቆይታ ያማረ በማድረግ የአካባቢው ሕብረተሰብ ከዘርፉ ገቢ እንዲያገኝ የሚያስችሉም ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የታደለችና በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ስንሄድ ያልተነኩ እምቅ ሀብቶች በስፋት የሚገኙባት ሀገር ነች። እነዚህ የተፈጥሮ ሃብቶች በአግባቡ ከታወቁ እና ጥቅም ላይ መዋል ከቻሉም የኢትዮጵያ የብልጽግና መሰረትና የሕዝቦቿም የኑሮ መሰረቶች ይሆናሉ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሰሞኑን በጅማና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብቶችን ሲጎበኙ ባስተላለፉት መልዕክት ‹‹ሀገሩን ያላወቀና ሀብቱን በአግባቡ ያልተጠቀመ የባከነ ነው›› ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

አባባሉ ትልቅ እውነት አለው፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያ ያላትን ዕምቅ የተፈጥሮ ሃብቶች በአግባቡ በማወቅ፣ በመጠቀምና በመጠበቅ ለትውልድ የሚተርፍ ሥራ መሥራት የእያንዳንዱ ዜጋ ግዴታ ሊሆን ይገባል፡፡ በየአካባቢው ያለውን እምቅ አቅም የተረዳ ዜጋ ለመገፋፋትና ለመጣላት የሚሆን ጊዜ ስለማይኖረው ለልማትና ዕድገት ይተጋል፡፡ ራሱን ቤተሰቡንና ሀገርንም ይለውጣል። በአጠቃላይ ያለንን እምቅ ሀብት ሥራ ላይ አውለን የኢትዮጵያን ብልጽግና ማረጋገጥ ይገባል፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎንም ለቱሪዝም ዘርፉ እንቅፋት የሆነውን ጦርናትና ግጭት በማስወገድ ኢትዮጵያ ያላትን ዕምቅ የተፈጥሮ ሃብቶችን እንድትጠቀም ማድረግ ም ወቅቱ የሚጠይቀው ትልቅ ጉዳይ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዛሬ ከትናንት እንዲሻል

ታምራት ተስፋዬ

የአይሁድ ዝርያና የደች ዜግነት ያለው ታዋቂው የፍልስፍልና ጠቢብ ባሩች ስፒኖዛ Baruch Spinoza ‹‹ If you want the present to be different from the past, study the past/ዛሬ ከትላንቱ የተሻለ እንዲሆን ከፈለግክ የትላንቱን በሚገባ አጢነው/››የሚል አባባል አለው፡፡ ይሕን አባባል በተለይ አዲስ ዓመትን ስንጀምር ይበልጥ ትርጉም ይሰጣል፡፡ ወደ አዲስ ዓመት ስንሸጋገር ካለፈው ልምድና ተግባራችን ትምህርት መቅሰም እንደሚገባን ያስገነዝባል፡፡

ይሁንና አንዳንዶች በአሮጌ ዓመት የሰሩትን ስህተት በአዲሱ ዓመትም ደግመው ሲሰሩ ራሳቸውን ያገኙታል። ይሕም ያለፈውን ልምዳቸውን የመለየትና ለመፍትሄ የመራመድ ፍላጎትም ሆነ ልምድ ስለሌላቸው የሚከሰት ስለመሆኑ እርግጥ ነው፡፡

ዛሬ ላይ ሆኖ የትላንት ተግባር ምን ጠቀመን? ስህተቱስት ምን አስተማረን? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትክክለኛውን መልስ ፈልጎ ማግኘት የቻለ ግን ከዚህ ቀደም የጨበጠው እሳት ዳግም እንደማይጨብጠው የሚያጠራጥር አይደለም፡፡፡

የዘመን በዘመን የጊዜ በጊዜ መተካት የማያቋርጥ ሂደት ቢሆንም አዲስ ዓመት ሰው ከራሱ ጋር ይታረቅ ዘንድ እቅዱ ከግቡ እንዲስማማ ውጫዊና ውስጣዊ ሕይወቱ እንዲጣጣም ወሳኝ ድርሻ አለው፡፡ አዲስ ዓመት የሰው ልጅ ራሱን የሚያሻሽልበት ያለፈውን ሕይወቱን ገምግሞ ደካማውን ሸሮ ጠንካራውን ይዞ እንዲቀጥልበት ለራሱ የፈጠረው የቀን ቀጠሮ ነው፡፡ አዲስ ዓመትም ራስን ለመለወጥ፣ አስተሳሰብን ለማደስ፣ አኗኗርን ለማስተካከል፣ ለማሰብና ለማሰላሰል እድል ይሰጣል፡፡ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ሰው ባሰመረው የጊዜ ድንበር ለአዲስ ዓመት ሁሌም አዲስ ያስባል፡፡

ኢትዮጵያውያንም 2015 ዓ.ም አሮጌ ብለው ሸኝተው አዲሱን 2016 ዓ.ም ተቀብለዋል፡፡ አዲስ ዓመትም በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ዘንድ አዲስ ቃል የሚገቡበት ዕለት ነው፡፡ ሁሉም በየፊናው መጪው ጊዜ መልካም እንዲሆን፤ ኑሮው እንዲሳካ ጎጆው እንዲሞላ፣ መንፈሱ እንዲረካ፣ አዕምሮው እንዲሰላ፣ ነፍስያው እንዲጠግብ፣ የውስጡም የውጪውም ሕይወቱ እንዲያምር ያቅዳል፡፡

ለአብዛኞቻችን ኢትዮጵያውያንም እውነተኛው የአዲስ ዓመት ትርጉሙም አዲስ ሰውነት፣ አዲስ አስተሳሰብ፣ አዲስ ለውጥ፣ አዲስ የሕይወት መንገድ የሚበጅበት፣ ለራሳችን ቀና አስተሳሰብ የምንቀይስበት በአጠቃላይ አዲስ የምንሆንበት የአዲስነት የጅማሮ ቀን ነው፡፡

አዲስነት የትላንቱን ድካም፤ ያለፈውን አጉል ልማድ መድገም ሳይሆን አዲሱን ኑሮ በአዲስ ሰውነት፣ በሰለጠነ አስተሳሰብና በቀናነት መጀመር ነው፡፡ አዲስነት በግንዛቤ መበልጸግ፣ በጥበብ መጎልመስ፣ ራስን በመቆጣጠር መርቀቅ ጭምር ነው፡፡

ዓመቱ አዲስ እንዲሆን ደግሞ አዲስ ሰው መሆንን የግድ ይላል፡፡ አዲስን ወይን ጠጅ በአሮጌ አቁማዳ ውስጥ እንደማይጨምሩት እና አዲሱና አሮጌው እንደማይስማሙ ሁሉ ሰው በአዲስነት ካልተቀበለው አዲስ ዓመትም የቁጥር ለውጥ ብቻ ይሆናል፡፡

ይሑንና በዘመን ሂደት በትውልድ ቅብብል የማይጠቅምን አስተሳሰብን ማራመድ እንደ አገርም ሆነ እንደ ህዝብ ጉዳቱ ግልፅ ነው። አንድ ከማድረግ ይልቅ የሚነጣጥል፤ መሰብሰብን ትቶ የሚበትን፣ ከማዋሃድ ይልቅ የሚለያይ አስተሳሰብን ማራመድ ኪሳራ እንጂ ትርፍም የለውም።

አንድ መታወቅ ያለበት ወሳኝ ጉዳይ ቢኖር ማሰብ መቻል ልዩ ፀጋ ነው። መልካምን ሃሳብን መርጦ መተግበር ደግሞ ሰው በራሱ ላይ የሚያመጣው በረከት ነው። ማንም ለሆዱ የሚስማማውን ምግብ እንደሚመርጠው ሁሉ ለአዕምሮውም የሚመጥን ሃሳብን መመገብ ራስን መጥቀም ነው።

ንፁህ ምግብ ሰውን ከበሽታ እንደሚከላከለው ሁሉ ንጹህና መልካም ሃሳብም ሰውን አፍራሽ ተልዕኮ ካለው ተግባር ያቅበዋል። ሰው ሃሳቡን እያበጠረ ገለባ ሃሳቡን የሚያስወጣበትና ጠቃሚውንና ፍሬ ሃሳቡን የሚያስቀርበት የሕሊና ወንፊት መስራት ይገባዋል። ሃሳብ እንደ ስንዴ አንክርዳዳድ ካልተጣራ ንጹሁንም ሃሳብ ያበላሻል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ትላንት በሃሳብ ቀድመው ከፍ ከፍ እንዳላልን ዛሬ አዲስ ሃሳብ መስራት፣ ሃሳቡን ማርቀቅ፣ ሃሳቡን ማጎልመስ፣ ሃሳቡን በተሻለ ሃሳብ መጣል፣ ሃሳቡን በሃሳብ ማድመቅ የሚያስችል ባህል ጠፍቶብናል። ትላንትም ሆነ ዛሬ እየተመላለሰ የሚደቁሰንና አዙሪት ሆኖብን ወደፊት አላንቀሳቅስ ያለን ችግራችንን በአስተሳሰብ ልእልና ተነጋግረንና ተወያይተን ፍቱን የሆነ መፍትሄ ማስቀመጥ አለመቻላችን ሆኖም ይታያል፡፡

በኢትዮጵያ ምድር ያለፈው ዓመት ደስታና ሀዘን ተስፋና ፍርሀት ድልና ትግል የተፈራረቁበት እንደነበር ይታወሳል፡፡ የምንሰማውና የምንናገረው የምንፈልገውን ብቻ ሆኖ በጥቂቱ አውቆ በብዛት መድምደም፣ በከፊል ሰምቶ በሙሉ መፍረድ፣ መርጦ በመመልከትና በመስማት ሳይመርጡ ማውገዝ የሁላችንም መገለጫ ሆኖም ታይቷል።

ይሕን ታሪክ በአዲስ ዓመት መለወጥ ይኖርብናል። ኢትዮጵያውያን በአዲሱ ዓመት ካለፈው ተምረን መጪውን ለማሳመር በተለይም አገር ሰላም እንድትሆን ካሳለፍናቸውም መልካም ሆነ እኩይ ታሪኮች ተምረን መጪውን ለማሳመር ማድረግ ያለብን ብዙ ነው፡፡

ኢትዮጵያችን በአዲስ ዓመት አዲስ አስተሳሰብ ያለው ዜጋን ትፈልጋለች፡፡ የሚከሳት አንጂ የሚከሳት አያስፈልጋትም፡፡ ዘመን የሚዋጅ፣ ትውልድን እንደ አዲስ የሚቀርፅ ትውልድ ትባጃለች፡፡ ትንሳኤዋን የሚሻ፣ ወደ ኋላ የሚጎትትና የማይጠቅም አስተሳሰብ በአዲስና በተሻለ አስተሳሰብ መለወጥ የሚችል ዜጋን ትናፍቃለች፡፡ ሊገነባ፣ ትውልድ ከፍ ከፍ ሊያደርግ የሚችል አስተሳሰብ ትሻለች፡፡

በአዲስ ዓመት ለመናቆር ሳይሆን ለመፋቀር ቦታ እንስጥ፡፡ ፀጉር ከመንጨት፣ ሃሳብ ማመንጨት እናስቀድም። ከመቆላለፍ መተላለፍን፣ ከመተናነቅ፣ መደናነቅን እንምረጥ። የአምናውን ዕዳ አንውረስ፡፡ የአምናውን ክፋት አንጨርስ፡፡ አዲስ ጎዳና ይተለም። አዳዲስ ፈትል ይቀለም፡፡ ተከፋፍሎ መፍረስ ይብቃ፡፡ ለቆጡ ተንጠራርተን የብብቱ አያምልጠን፡፡

የእብደቱ መንገድ ቁልቁለቱ፣ በዘር ሀረግ መለቃቀም፣ በእምነት ጥላ መጠቃቀም ይብቃን፡፡ በሰውነት እንከባበበር። ማድላት ማግለል እንቅበር። ቅን እናስብ። ቅን እንናገር፡፡ አፍና ልባችን አንድ ይሁን፡፡

በአዲሱ ዓመት በአስተሳሰብ ለውጥ ‹‹እኛ እነሱ››፣ ‹‹የእኛና የእነርሱ››የሚል ዘረኛ ቀይ የጎጥ መስመር ከማጋደም እንቆጠብ፡፡ በብሄር መነፅር ተሸፍነን ‹‹እንዲህ ነን››ስላልን ‹‹እንዲያ››እንደማንሆን እንገዘብ፡፡ የባንዲራ ክብር ይታየን። በጎጥና መንደር የጠበበ ሰው አስፍቶ ማሰብ ይሳነዋልና ከጎጥ አስተሳሰብ እንገንጠል፡፡

ምግባርና ተግባር የጎደለን፣ የሚጨበጥና የሚያዝ የሌለን አንሁን፡፡ ህሊና ያድሰን፡፡ ሰውነት ይመልሰን። ሃይማኖት ይፈውሰን፡፡ የሀገር ፍቅር ድምጽ ይሠማን። ሁሉም ወቃሽ ከመሆን እንቆጠብ፡፡ ‹‹ተበድያለሁ›› ከሚል በደል ቆጣሪነት እንፋታ፡፡ ከተገፊነት ተረክ እንላቀቅ። ከሚያነቃቅፈን ይልቅ የሚያስተቃቅፈንን እንምረጥ፡፡ ቃልና ተግባራችን ይመጣጠን፡፡

በአዲስ ዓመት ባለፈውና ባሳለፍነው አጉል ጊዜ መቆጨትን ማቆም እና ለወደፊቱ መሻልን ማሰብ ልንጀምር ይገባል፡፡ ከማፍረስ ይልቅ መካብ ሊቀለን፣ ሃሳብ ልዩነት ሁሌም ሊገለን ይገባል። ኋላቀርነት ሊማርከን፣ መጥፎ ታሪክ ሊጎትተን፣ ዘመን ሊያድሰን፣ ክፉ ትናንት ሊቀይረን አይገባም፡፡ ከመጥበብ መስፋትን እንምረጥ፡፡ ለሕዝብ የማይበጅ የሴራ ፖለቲካ መጎንጎን ማቆም አለብን፡፡

በአዲስ ዓመት በዚህ አስተሳሰብ ለመቃኘትና አስተሳሰቡን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ ለዚህ የሚመጥን ጭንቅላት መፍጠር ግድ ይለናል። አስተዋይ ጭንቅላት አንድም ከመጽሐፍ ማሕፀን በንባብ ምጥ የሚወለድ፤ አንድም ትላንትን በማስተዋልና የኋላ ታሪክን ተጠቅሞ በበጎ እሳቤ በመለወጥ እውን እንደሚሆን ልንረዳም ይገባል፡ ፡ ይህ ማድረግ ከቻልን የተሻለችና በሁሉም መስኮች የተሳካላት ኢትዮጵያን ማየት ህልም አይሆንብንም፡፡

አዲሱ ዓመት ምንም ልንለውጠው ከማንችለው ትናንት ይልቅ የምንፈልገውን ነገር ሁሉ ልናደርግበት በምንችልበት ነገ ላይ እንረባረብ፡፡ ስለትናንትና አበክረን ስንናገር ዛሬና ነገ እንዳያመልጡን እንንቃ፡፡ መጪው ዓመት ያለፈውን እያስታወስንና እያወሳን የምንጋጭበት ሳይሆን መጪውን እያለምንና እየተለምን በአንድነት በፍቅር ተደምረን የምንፈስበት ጨርሶ የመጀመር ዓመት ይሁንልን፡፡

# ተጠየቅ

# "እያንዳንዱ ሠራተኛችን የራሱ የሆነ የፖለቲካ ዕይታ፣ ሃይማኖትና ብሔር ሊኖረው ቢችልም፤ ከነዚህ ሁሉ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ሙያዊ በሆነ መንገድ ሥራዎችን ይሠራል"

**- ዶክተር እንዳለ ኃይሌ፣**
**የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ዋና እንባ ጠባቂ**



**በስጥሻቸው ልዑልሰገድ**

የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በሁለት አዋጆች (በማቋቋሚያ አዋጅ 1142/2011 እና በመረጃ ነፃነት አዋጅ 590/2000) መሰረት ስልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቶት የተቋቋመ የዴሞክራሲ ተቋም ነው:: በእነዚህ አዋጆች መሰረትም በአጠቃላይ በመልካም አስተዳደር ስራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ፣ እንደ ሀገር በመንግስታዊ ተቋማት ውስጥ የመልካም አስተዳደር ሥርዓት እንዲሰፍን ማስቻል ተቀዳሚ ሥራው ነው::

በተያያዘም ከመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ እና ከመልካም አስተዳደር አንፃር ልዩ ልዩ ጥናቶችን በማድረግ ለመንግስት ምክረ-ሃሳብ ይሰጣል:: እኛም በዛሬው የተጠየቅ ዓምዳችን የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ይሄን ኃላፊነቱን ከመወጣት አንጻር የ2015 በጀት ዓመት እቅድና ክንውኑን መነሻ በማድረግ በሌሎች ተቋማዊ እንቅስቃሴዎቹ ዙሪያ ከተቋሙ ዋና እንባ ጠባቂ ዶክተር እንዳለ ኃይሌ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበናል::

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ ከተሰጠው ተልዕኮ አኳያ በ2015 በጀት ዓመት በያዘው እቅድ መሰረት ምን ያህል በውጤታማነት የሚጠቀሳቸው ስራዎችን ሰርቷል?**

**ዶክተር እንዳለ፡-** የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በአዋጅ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት መሰረት በማድረግ 13 ግቦችን ለይቶ ስራዎችን ሰርቷል። ከነዚህ ውስጥ በዋናነት ተቋሙ የተቋቋመለት አንዱ ስራ፣ በመንግስት አስፈፃሚ አካላት የደረሱ የአስተዳደር በደሎችን መርምሮ የመፍትሄ ሀሳብ መስጠት ነው::

በዚህ ረገድ በተቋማችን በ2015 የበጀት ዓመት በእቅድ ደረጃ የተያዘው አምስት ሺህ 800 አቤቱታዎችን ለመቀበል ነበር:: ነገር ግን ሰባት ሺህ 416 አቤቱታዎችን ተቀብለናል። ይህ ቁጥር በመዝገብ ጀረጃ የተቀበልነው ሲሆን፤ በግለሰብ ደረጃ 277 ሺህ 698 ዜጎች ለተቋማችን አቤቱታቸውን አቅርበዋል:: ከዚህ ውስጥ ደግሞ ከ100 ሺህ በላይ አቤቱታዎች የቤት ፈረሳን የሚመለከቱ ናቸው::

በአጠቃላይ ከቀረቡት አቤቱታዎች መካከል በተቋማችን ስልጣንና ኃላፊነት ሊፈቱ የሚችሉ አንድ ሺህ 844 አቤቱታዎች ተቀባይነት ያገኙ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥም በበጀት ዓመቱ ለአንድ ሺህ 601 አቤቱታዎች እልባት ተሰጥቷል:: የተቀሩት አቤቱታዎች ምርመራቸው ባለመጠናቀቁ ለ2016 በጀት ዓመት የተላለፉ ሲሆን፤ አንዳንድ መዝገቦች በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ተፈፃሚ የሚሆኑና በሂደት ላይ ያሉ ናቸው::

ለተቋማችን የሚቀርቡ አንዳንድ አቤቱታዎች ምርመራ ሳያስፈልጋቸው አቤቱታ ከቀረበባቸው ተቋማት ጋር በመነጋገር የሚፈቱበት ሁኔታ አለ:: ይህንን early resolution ብለን እንጠራዋለን:: ሌሎች አቤቱታዎችንም በደል መፈፀሙን ካረጋገጥን በኋላ ምርመራ አድርገን የመፍትሄ ሃሳብ እንሰጥባቸዋለን::

በበጀት ዓመቱም እልባት የሰጠንባቸው ጉዳዮች በዋናነት ከስራ ጋር የሚያያዙ አቤቱታዎች፣ የጡረታ ማስከበር አቤቱታ፣ ከመሬት ጋር የተያያዙ የይዞታ አቤቱታዎች፣ የአገልግሎት አሰጣጥ አቤቱታዎች እና የመረጃ ነፃነትን የተመለከቱ አቤቱታዎች ናቸው::

ተቋማችን ባደረገው ምርመራ እና በሰጠው የመፍትሄ ሃሳብ አንድ ሺህ 332 ሰዎች ወደ ስራ ገበታቸው እንዲመለሱ፤ ያልተከፈላቸው የወር ደሞዝ እንዲከፈላቸው እና የደረጃ እድገት የሚገባቸው ሰራተኞችም እድገት እንዲሰጣቸው ተደርጓል::

ከካሳና ምትክ ጋር ተያይዞ አቤቱታ ያቀረቡ 32 ግለሰቦች ካሳ እና ከ250 እስከ 500 ካሬ ሜትር ምትክ ቦታ እንዲሰጣቸው አድርገናል:: ከጡረታ ጋር በተያያዘ 28 ሰዎች የጡረታ መብታቸው እንዲከበርላቸው አድርገናል:: ሁለት መቶ አቤቱታ አቅራቢዎች ከህግ ውጪ የተከለከሉትን ልዩ ልዩ መንግስታዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል::

በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ የመፍትሄ ሃሳብ የተሰጠባቸው ጉዳዮች እስከ ሰኔ ወር ድረስ 60 ነጥብ ሶስት በመቶ የሚሆነው የመፍትሄ ሃሳብ ተፈፃሚ ሆኗል:: የተቀሩትም የተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ስላላቸው በዚያ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናሉ::

ሌላው እንደተቋም በአዋጅ የተሰጡን ስራዎች፣ የምርመራ ስራዎችን ማከናወን፣ የቁጥጥር ስራዎችን ተግባራዊ ማድረግ እና ልዩ ልዩ ጥናቶችን መስራት ነው:: በተጨማሪም ስልታዊ ምርመራዎችንም እናካሂዳለን::

ከዚህ በመነሳት የአስተዳደር በደልን ከመከላከል አንፃር በበጀት ዓመቱ 52 ጉዳዮች ላይ የቁጥጥር ስራ ለመስራት አቅደን የነበረ ሲሆን፤ 46 ጉዳዮች ላይ ቁጥጥሩን ተግባራዊ ማድረግ ችለናል:: ይህንን በተቋም ደረጃ 153 ተቋማት ላይ መደበኛ ቁጥጥር ለማድረግ አቅደን 164 ተቋማት ላይ በ46 ጉዳዮች ዙሪያ ቁጥጥር አድርገናል::

አቤቱታ አቅራቢዎች ቅሬታ ከሚያቀርቡባቸው ጉዳዮች በመነሳት፤ ቅሬታ የሚበዛባቸውን ጉዳዮችና ተቋማት በመለየት የምርመራ ስራ እናከናውናለን። ባለፉት ዓመታት ከመንግስት የግዢ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ምን ያህል ግልፀኝነት የሰፈነበት ነው የሚለውን መሰረት በማድረግ ምርመራ አካሂደናል::

ምክንያቱም አብዛኛው የመንግስት ተቋማት ግዢ የሚካሄደው በዚህ ተቋም አማካኝነት ነው። ይህ ተቋም ነጋዴዎችን በምን አይነት አግባብ ነው የሚለየው፣ ምን አይነት የግዢ ስርዓት ይከተላል፣ ከደንበኞች ምን አይነት ቅሬታ ይቀርባል የሚለውን መሰረት አድርገን ቁጥጥር አካሂደናል::

በተመሳሳይ፣ አሁን ካለው የኑሮ ሁኔታ አንፃር መንግስት ከፍተኛ ድጎማ እያደረገ የሚቀርቡ በርካታ የፍጆታ እቃዎች አሉ:: እነዚህ በድጎማ የሚቀርቡ የፍጆታ እቃዎች በአግባቡ ለተጠቃሚ ሕብረተሰብ እየቀረቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን በሚኒስቴር፣ በንግድ ቢሮ፣ በክፍለ ከተማ እና በወረዳ ደረጃ ምን ያህል እየተቆጣጠረ ይገኛል የሚለውን የቁጥጥር ስራ አድርገናል::

ከሀገራዊ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ በትግራይ፣ በአማራ እና በአፋር ክልሎች በነበረው ጦርነት ምክንያት የተፈናቀሉ ዜጎች አሉ:: እነዚህ የተፈናቀሉ ዜጎችን ሰብዓዊ እርዳታ ከማቅረብ አንፃርና መልሶ ከማቋቋም ረገድ ምን እየተሰራ እንደሆነ ቁጥጥር አካሂደናል። በሌላ በኩል በኦሮሚያ፣ ሶማሊያና በደቡብ ክልል የተለያዩ ዞኖች ድርቅ የተከሰተባቸው አካባቢዎች አሉ። በእነዚህ አካባቢዎች የሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦትና መልሶ ከማቋቋም ረገድ ምን ስራዎች ተሰርተዋል በሚል የቁጥጥር ስራዎችን ሰርተናል።

ሌላኛው፣ ለተቋማችን የተሰጠው ስልጣን ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ሴቶች፣ ህፃናት፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች በዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች የተሰጣቸው እና ኢትዮጵያም ተግባራዊ ለማድረግ የፈረመቻቸው መብቶች አሉ። እነዚህ መብቶች በሕገ መንግስቱም ተካተው የሚገኙ ናቸው::

የተለያዩ ተቋማትም እንደየስራ ባህሪያቸው የሚያወጧቸው የስራ መመሪያዎች ይገኛሉ:: እነዚህ መመሪያዎች ምን ያህል በአግባቡ እነዚህን የሕብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ አድርገዋል የሚለውን እንመረምራለን። ለአብነትም፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጀት በሚመድብበት ወቅት እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ አድርጓል ወይ? መንገድ ትራንስፖርት እንዲሁም ስራና ከተማ ልማት፣ እቅድ በሚያቅዱበትና በጀት በሚመድቡበት ወቅት እነዚህን የማህበረሰብ ክፍሎች ምን ያህል ታሳቢ ያደርጋሉ? በአጠቃላይ ለነዚህ የማሕበረሰብ ክፍሎች የተሰጡ መብቶችስ ምን ያህል ተፈፃሚ ናቸው የሚለውን የመከታተልና የመቆጣጣር ኃላፊነት ለተቋማችን ተሰጥቶታል::

በዚህ ረገድ በበጀት ዓመቱ በአንድ መቶ 28 ተቋማት ላይ በ49 ጉዳዮች ዙሪያ ቁጥጥር እናደርጋለን ብለን አቅደን የነበረ ሲሆን፤ በ36 ጉዳዮች ዙሪያ አንድ መቶ 57 ተቋማት ላይ ቁጥጥር አድርገናል::

ልዩ ትኩረት ከሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎች አንፃር አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ተቋማት ምን ያህል ተደራሽነት እንዳላቸው ቁጥጥር አድርገናል:: በዚህም የተገነዘብነው ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጀምሮ የክፍል ደረጃቸው እየጨመረ በሚሄድበት ቁጥር ትምህርት የማቋረጥ ምጣኔው እየጨመረ እንደሚሄድ ነው።

ለዚህ ዋና ምክንያቱ ደግሞ ትምህርት ቤቶቹ ለነዚህ የማሕበረሰብ ክፍሎች ድጋፍ ማድረግ የሚችሉበት ብቁ የሰው ኃይል የላቸውም:: የትምህርት ቤቶቹ መሰረተ ልማቶችም ለነዚህ ተማሪዎች ምቹ ሆነው አልተሰሩም። ከዚህ በተጨማሪም አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በአግባቡ ስለማይስተናገዱና በሌሎች ተማሪዎች መገለል ስለሚደርስባቸው ለማቋረጥ ይገደዳሉ::

በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም ከሌሎቹ የተሻሉ ናቸው በሚባሉት በሀዋሳ እና በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ባደረግነው ቁጥጥር እንዳየነው፤ ሁለቱም ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ለአይነ ስውራን የሚሆን ምቹ መንገድ የላቸውም። የመማሪያ ክፍሎቹም ቢሆኑ አካል ጉዳተኞችን ማዕከል ያደረጉ አይደሉም። የሚደረግላቸው ልዩ ድጋፍ አናሳ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲ ከደረሱ በኋላ በርካቶች ለማቋረጥ ይወስናሉ::

የመረጃ ነፃነት አዋጅ ተግባራዊ እንዲሆን ለተቋማችን ሶስት መሰረታዊ ኃላፊነቶች ተሰጥተውታል። እነዚህም አንደኛ ግንዛቤ ማሳደግ፤ በተለይም በአዋጁ መረጃ እንዲሰጡ በየተቋማቱ ኃላፊነት የተሰጣቸው ለሕዝብ ግንኙነት ሰራተኞች እንደመሆኑ መጠን ለነሱ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ይሰራል:: ሁለተኛ አዋጅ ቁጥር 590/2000ን ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ የሕግ ማዕቀፎች እናዘጋጃለን:: ሶስተኛ የመረጃ ነፃነትን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ተቋማት ምን እየሰሩ ነው የሚለውን የቁጥጥር ስራ እንሰራለን::

በዚህም የመረጃ ነፃነት መብት አዋጁ በሚፈቅደው ልክ ተግባራዊ እየተደረገ እንዳልሆነ ባደረግነው ቁጥጥር ስራ ለማወቅ ችለናል:: የመንግስት አስፈፃሚ አካላት በእጃቸው ያለውን መረጃ የመገናኛ ብዙሃንን ጨምሮ ለሚጠይቋቸው ዜጎች መስጠት እንዳለባቸው አዋጁ ያስገድዳል:: ነገር ግን ይህንን ባለማድረጋቸው ከበርካታ የመገናኛ ብዙሃን ቅሬታ ያቀርባሉ::

ከዚህ አኳያ በበጀት ዓመቱ የመረጃ ነፃነት የሚመለከቱ 141 አቤቱታዎች ለተቋማችን ቀርበዋል። እነዚህ አቤቱታዎች የመገናኛ ብዙሃንን ጨምሮ ለተለያዩ የምርምር ስራዎች መረጃ ጠይቀው በተከለከሉ ግለሰቦች የቀረቡ ጥያቄዎች ናቸው::

የመረጃ ነፃነት አዋጁ የመገናኛ ብዙሃን መረጃ በጠየቁ በ10 ቀናት ውስጥ፤ እንዲሁም ማንኛውም ዜጋ በ30 ቀን ውስጥ የጠየቁትን መረጃ የማግኘት መብት እንዳላቸው ያስቀምጣል። ሆኖም ለመገናኛ ብዙሃን የተቀመጠው የአስር ቀን ገደብ መረጃን በወቅቱ ወደ ማሕበረሰቡ እንዳያደርሱ የሚያደርግ ነው:: ይህንን መሰረት አድርገን አዋጁ በራሱ ክፍተት እንዳለበት በመመርመር እንዲሻሻል ሃሳብ አቅርበናል::

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህን ሥራዎች በማከናወን ሂደት ምን ያህል ተደራሽ ሆነናል ብላችሁ ታምናላችሁ?**

**ዶክተር እንዳለ፡-** በሀገራችን ያለው የሰላም ሁኔታ ሁሉም ቦታ ተደራሽ ለመሆን እንዳንችል ተግዳሮት ሆኖብን ቆይቷል:: ኃላፊነት ለመውሰድም ሆነ ስምሪት ለመስጠት አዳጋች ሁኔታዎች ነበሩ። ለአብነትም ኦሮሚያ ክልልን መጥቀስ እንችላለን:: ስራዎቻችንን እየሰራን ያለነው ማዕከላዊ ኦሮሚያ ላይ ትኩረት አድርገን ነው::

ላለፉት አራት ዓመታት ወደ ምዕራብ ወለጋ በመሄድ ስራችንን መስራት አልቻልንም:: በአካባቢው ያለው የሰላም ሁኔታ አስተማማኝ ስላልሆነ ባለሙያዎቻችንን ወደ ቦታው መላክ አልቻልንም። ባለፉት ዓመታት ስራችንን እንዳንሰራ ተግዳሮት ከሆኑብን ችግሮች መካከልም ይሄ በዋናነት የሚጠቀስ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ የተፈተነባቸውን ጉዳዮች ካነሱ አይቀር ተቋሙ በአዋጅ የተሰጡትን ኃላፊነቶች ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እንዳያደርግ እያጋጠሙት ያሉ ተግዳሮቶች ምንድናቸው?**

**ዶክተር እንዳለ፡-** ተቋሙ በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ ትግባራዊ እንዳያደርግ በርካታ ተግዳሮቶች ይገጥሙታል:: ከነዚህ መካከልም በሀገሪቱ ያለው የዴሞክራሲ ባህል ደካማ መሆን ተጠቃሽ ነው:: እንደ እንባ ጠባቂ ተቋም ያሉ ተቋማት ስራቸውን በአግባቡ ለማከናወን እና ውጤታማ እንዲሆኑ መንግስታዊ ተቋማት የዴሞክራሲ እሴቶችን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው። የዴሞክራሲ ባህላችንም ማደግ አለበት። አሁን ባለንበት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

ከገጽ 6 የዞረ

## “እያንዳንዱ ሠራተኛችን የራሱ የሆነ የፖለቲካ ዕይታ፣ ...

የሀገራችን የፖለቲከ ሁኔታ የዴሞክራሲ ባህላችን ደካማ ነው። የዜጎችን መብት አክብረው የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት የሚሰጡ መንግስታዊ ድርጅቶችም አነስተኛ ናቸው፡፡

ምክንያቱም “መንግስት በግልጸኝነትና በተጠያቂነት መርሆች መሰረት ስራውን እየሰራ ነው ወይ? የትኛው የመንግስት ስራ አስፈፃሚ አካል ስራውን በአግባቡ ባለመስራቱ ከስልጣኑ እንዲነሳ ተደረገ? የመንግስት ስራ አስፈጻሚ አካላት ስራቸውን በግልጸኝነት ያከናውናሉ ወይ? ማህበረሰቡንስ ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ያስተናግዳሉ?” የሚሉት ጉዳዮች ሁሉ በዴሞክራሲ ስርዓት ማደግ ጋር የተገናኙ ናቸው።

ሌላኛው ለተቋሙ ተግዳሮት የሆነበት ጉዳይ፤ ከመንግስት ለስራ ማስኬጃ የሚመደብለት በጀት አነስተኛ መሆን ነው፡፡ ለተቋሙ ሰራተኞች የሚከፈለው የደመወዝ ክፍያ ዝቅተኛ መሆንም ሰራተኛው ረጅም ጊዜ በተቋሙ እንዳይቆይ አድርጎታል፡፡ የስራ ልምድ ለማግኘት ብቻ የሚቀጠሩ ከቆይታ በኋላ ድርጅቱን የሚለቁ ሰራተኞች በርካታ ናቸው፡፡ ይህ በመሆኑ ተቋሙ በርካታ ልምድ ያላቸው ሰራተኞችን ለማቆየት አልቻለም፡፡

ሌላውና ትልቁ ችግር ደግሞ፣ ተቋሙ የሚሰጣቸው የመፍትሄ ሀሳቦች የሚተገበሩት በመንግስት አስፈፃሚ አካላት በጎ ፍቃደኝነት ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው ነው፡፡ የተቋሙ ስራ የመፍትሄ ሃሳብ መስጠት ነው፤ ይህ የመፍትሄ ሃሳብ ግን የሕግ አስገዳጅነት ባህሪ የለውም። የሕግ አስገዳጅነት ባህሪ የለውም ስንል ግን ተጠያቂ አያደርግም ማለት አይደለም፡፡ ተጠያቂ የምናደርግባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ፡፡

የሌሎች ሃገራትን ልምድ ስንመለከት እንደ እንባ ጠባቂ ተቋም ያሉ የዴሞክራሲ አካላት የሚሰጧቸው የመፍትሄ ሃሳቦች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተግባራዊ ይደረጋሉ። በሀገራችን ግን ተፈፃሚነቱ ቅድመ ሁኔታ የበዛበትና አስፈፃሚ አካላት ተባባሪ የማይሆኑበት ሁኔታ ስላለ ችግር ሆኖብናል፡፡ እነዚህን መሰል ጉዳዮች ናቸው በበጀት ዓመቱ ውስጥ ስራዎቻችንን ለመስራት በዋና ዋና ተግዳሮት ሆነው የሚገለጹት፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ በችግርነት ካነሷቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የአስፈጻሚ አካላት ተባባሪነትን ይመለከታል፡፡ በዚህ ረገድ ተቋማችሁ ስራውን በተሳካ መልኩ እንዲሰራ የመንግስት አስፈፃሚ አካላት እገዛ ምን ሲሆን ይገባዋል?**

**ዶክተር እንዳስ፡-** በአዋጃችንም ሆነ በዓለም አቀፍ መርሆች የሚያስቀምጡት፤ የመንግስት አስፈፃሚ አካላት፣ የዴሞክራሲ ተቋማት በተለይም ከሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የሚሰጡትን የመፍትሄ ሀሳቦች የመተባበር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

የመተባበር ኃላፊነት አለባቸው ሲባል፤ ሕገመንግስቱም ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው የመንግስት ተቋማት በግፀኝነትና በተጠያቂነት መርህ መሰረት መስራት አለባቸው፡፡ እነዚህ መንግስታዊ ተቋማት ስራቸውን የሚሰሩት ከሕዝብ በሚሰበሰብ ግብር ነው። ስለዚህ ለግብር ከፋዩ ሕብረተሰብ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት በአግባቡ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

አንዳንድ ተቋማት ይህንን ግዴታቸውን በመዘንጋት በእነሱ ፍቃድ ላይ የተመሰረተ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ይመስላቸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ በ2016 በጀት ዓመት መንግስት ትኩረት ሊያደርግባቸው ይገባል ብለን የለየነው፤ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንን መሰረት አድርገው የተዋቀሩ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮዎች አሉ፡፡ በእነዚህም የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ፕሮግራምን የበለጠ ማጠናከር ይኖርበታል፡፡

ለአብነት፣ አብዛኛው የመንግስት ተቋማት በተለይ ገቢ ከሚያመነጩ ስራዎች ጋር የተያያዙ ተቋማት ከፍተኛ የሆነ ብልሹ አሰራር እንደሚስተዋልባቸው በቁጥጥር የለየናቸው ተቋማት አሉ፡፡ የመንግስት ተቋማት ከሕዝብ በሚሰበሰብ ታክስ የሚተዳደሩ እንደመሆናቸው መጠን የሕብረተሰቡን ፍላጎት መሰረት ያደረገ አገልግሎት መስጠት አለባቸው። ይህንን ሳያደርጉ ቀርተው ወደ ተቋማችን የሚመጡ አስተዳደራዊ በደሎችን መርምረን ተቋማቱ የመፍትሄ ሃሳብ የማስጠት ኃላፊነት አለብን፡፡ ስለዚህ ይህንን በመፈፀም ረገድ የመንግስት አስፈፃሚ አካላት ኃላፊነትም ግዴታም ያለባቸው መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ መልኩ በሥራ አስፈጻሚው**



**ተጽዕኖ ያስ ከመሆኑ አንጻር በተቋማት ምላሽ የማይሰጥባቸውን ጉዳዮች ለይቶ ምላሽ በማይሰጡ የመንግስት ተቋማት ላይ ክስ ከመመስረትና ጉዳዩን ስሚመለከተው አካልም ሆነ ለሕዝብ ከማሳወቅ አንፃር ምን የተሰሩ ስራዎች አሉ?**

**ዶክተር እንዳስ፡-** የሚሰጣቸውን የመፍትሄ ኃሳቦች የማይፈፅሙ አካላት ካሉ አንደኛው መንገድ ክስ መመስረት ነው፡፡ ሌላኛው፣ ደግሞ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሌርፖርት እናቀርባለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በመገናኛ ብዙሃን የማጋለጥ ስራ እንሰራለን፡፡

በዚህም በ2015 በጀት ዓመት የተሰጣቸውን የመፍትሄ ሀሳብ ተግባራዊ ባላደረጉ ሶስት የመንግስት አስፈፃሚ አካላት ላይ በልዩ ሪፖርት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርበናል። እነዚህ ተቋማትም፤ የፌደራል ጉምሩክ ኮሚሽን፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እና የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ናቸው፡፡

ለምሳሌ፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እና የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን አባላት የሰባት ዓመታት አገልግሎት ካጠናቀቁ በኋላ መልቀቂያ የማግኘት መብት አላቸው። ይህ የፖሊስ አባላት መብት ነው። ይህንን ደንብ በመተላለፍ መልቀቂያ የሚከለክሉ ተቋማት አሉ፤ በተለይም የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እና የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን፡፡ ስለዚህ እነዚህ ተቋማት ከእኛም አቅም በላይ ስለሆኑ እና በተደጋጋሚ በአካልም ውይይት አካሂደን፣ በርካታ የደብዳቤ ምልልሶችንም አድርገን ለማስተካከል ፍቃደኛ ስላልሆኑ በልዩ ሪፖርት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ልከናል፡፡

ከፌደራል ጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በተያያዘ፤ ማንኛውም ሰው ወደ ሀገር ውስጥ በሚገባበት ወቅት የግል መገልገያ እቃዎችን ይዞ የመግባት መብት አለው። ነገር ግን ይህ መብት በእቃው አይነት አልተለየም፤ በዓመት ምን ያህል ጊዜ ማስገባት እንደሚቻል አልተገለፀም፤ መግባት የሚችለው የእቃ መጠንም በቁጥር አልተቀመጠም፡፡

ይህንን ክፍተት እንዲያስተካክል ለኮሚሽኑ አሳውቀን መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡ ይህንን ማድረጉ የሚበረታታ ነው። ነገር ግን ይህ መመሪያ ከመዘጋጀቱ በፊት ከ300 በላይ አቤቱታዎች ወደ ተቋማችን መጥተዋል፡፡ ይህ መመሪያ ግን በነዚህ ሰዎች ላይ ተግባራዊ አይሆንም ተገዢም አያደርጋቸውም፡፡ ስለዚህ የተወረሰባቸው ንብረት እንዲመለስላቸው ብለን የመፍትሄ ሀሳብ ብንሰጥም አልፈፀመም፡፡ በዚህ ምክንያት ተቋማችን ተጠሪነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመሆኑ በልዩ ሪፖርት አስተላልፈናል።

ከዚህ ባለፈ፣ ተቋማችን ሰባት የክልል ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቶች አሉት፡፡ በእነሱ አማካኝነት 11 ጉዳዮች ላይ ክስ እንዲመሰረትባቸው ወደ ፍርድ ቤት ልከናል። ሁለት ጉዳዮች ላይ በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት የማጋለጥ ስራ ሰርተናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ በሥራ ሂደት የሚገጥሙት ፈተናዎችንም ሆነ ከአስፈጻሚ አካላት ጭምር የሚመጡበትን ጫናዎች ተቋቁሞ የመስራት ሁኔታው ምን ይመስላል?**

**ዶክተር እንዳስ፡-** ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ባለው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ የዴሞክራሲ ተቋማት እንደልባቸው የሚሰሩበት አውድ የለም፡፡ ፖለቲካዊ ጫና፣ የበጀት ጫና እና በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ተንቀሳቅሶ መስራት አለመቻልን የመሳሰሉ ጫናዎች አሉ፡፡ እነዚህ ጫናዎች ተቋሙ መስራት በሚፈልገው ልክ እንዳይሰራ እንቅፋት ሆነውበታል። ቢሆንም ተቋማችን እነዚህን ጫናዎች ተቋቁሞ ያቀዳቸውን እቅዶ 85 በመቶ ለማሳካት ችሏል፡፡

ሌላው መታወቅ ያለበት ተቋማችን የተለያዩ ጫናዎች ቢኖሩበትም፣ ነፃና እና ገለልተኛ ሆኖ ከመስራት አንፃር ከየትኛውም የመንግስት ወገን ጣልቃ ገብነት የለበትም። እያንዳንዱ ሰራተኛም የራሱ የሆነ የፖለቲካ እይታ፣ ሀይማኖትና ብሄር ሊኖረው ቢችልም፤ ከነዚህ ሁሉ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ሙያዊ በሆነ መንገድ ስራዎችን ይሰራል። የመንግስት አስፈፃሚ አካላት በስራችን ጣልቃ የመግባት ሁኔታም አነስተኛ ነው፤ ይህ መሆኑ ለኛ ትልቅ እድል ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ በአዋጅ የተሰጠው ስልጣንና ተግባር ላይ የተደረገው ማሻሻያ በስራችሁ ላይ የፈጠረው ለውጥ አለው?**

**ዶክተር እንዳስ፡-** በ2011 ዓ.ም በፊት ከነበረው ስልጣንና ተግባር ላይ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በፊት ተቋሙን የሚመሩ አመራሮችን መርጦ በቦታው ላይ ያስቀምጥ የነበረው ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ነው፡፡ የተቋሙ ሰራተኞች አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲ አባል የነበሩ ሲሆን ሁለት ኃላፊዎች የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የነበሩ ናቸው። አዋጁ ከተሻሻለ በኋላ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የነበሩ ከአባልነታቸው እንዲለቁ ተደርጓል፡፡ በተቋሙ ውስጥ የነበሩ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ አባል የነበሩ ሰራተኞች ከአዋጁ መሻሻል በኋላ ከአባልነታቸው እንዲለቁ ተደርጓል፡፡

በአዋጁ በግልፅ እንደተቀመጠው የተቋሙ አመራር የየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን እንደሌለበትና ነፃና ገለልተኛ ሆኖ መስራት እንዳለበት አስቀምጧል፡፡ በ2011 ዓ.ም የተሻሻለው ይህ አዋጅ ተቋሙ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ መስራት የሚያስችለውን አቅም ሰጥቶታል፡፡ በቀጣይም ተቋሙ ተጨማሪ አቅም እንዲኖረው እና ተደራሽነቱን ለማስፋት እንዲያስችል ተጨማሪ ማሻሻዎች እንዲደረጉበት ጠይቀን ምላሽ በመጠበቅ ላይ እንገኛለን፡፡

እስካሁን ስንሰራ የነበረው በመንግስት አስፈፃሚ አካላት የሚፈፀሙ አስተዳደራዊ በደሎች ላይ ብቻ ነው፡፡ በቀጣይ አዋጁ ሲሻሻል በመንግስት ተቋማት ላይ ብቻ ሳንወሰን በትላልቅ የግል ተቋማት ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችንም ማስተናገድ እንድንችል ያግዘናል፡፡

ምክንያቱም፣ ባለው ሁኔታ በተመረጡ ትላልቅ የግል ተቋማት ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎች አሉ። ለምሳሌ፤ አበባ እርሻ ላይ ከደመወዝ ጋር ተያይዞ፤ እንዱስትሪ ፓርኮችም ከጉልበት ብዝበዛ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ቅሬታዎች አሉ። ኣዋጁ ሲሻሻል ይህንን ማስተናገድ የምንችልበት ስልጣንና ኃላፊነት ይሰጠናል ብለን እንገምታለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ ካለፉት ካለፈው ሂደት (ከድክመቱም፣ ከጥንካሬውም) ተምሮ በቀጣይ ተልዕኮውን የሚመጥን ሥራን ከመስራት አኳያ ምን አስባል?**

**ዶክተር እንዳስ፡-** ከባለፉት ዓመታት ልምዶቻችን አንዳንድ ሀገራዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ትኩረት የሚፈልጉ መሆናቸውን ተምረናል፡፡ ስለዚህ እነዚህን የእቅዳችን አካል አድርገን እንዲሰራ አድርገናል፡፡ ከዚህ በፊት እርምጃ የምንወስደው ክስተቶቹ ሲከሰቱ ብቻ ነበር። ለአብነት፤ በአንድ አካባቢ ላይ መፈናቀል ይኖራል። ከመፈናቀላቸው በፊት መንግስት የሕግ የበላይነትን ማስከበር ያልቻለው ለምንድነው፣ ከተፈናቀሉ በኋላስ መንግስት ለነዚህ ተፈናቃዮች ምን አደረገ የሚለውን የምናየው ጉዳዩ ከተከሰተ በኋላ ነበር፡፡

ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ግን የሚከሰቱ ወቅታዊና ሀገራዊ ጉዳዮች በማለት ለይተን ከሁለት እስከ ሶስት የሚደርሱ ጉዳዮችን ማየት እንዳለብን የእቅዳችን አካል አድርገናል፡፡ ይህንን የእቅዳችን አካል አድርገናል ስንል ለዚህ ታሳቢ የሚሆን በጀትም እንመድባለን ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ፣ የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮችን የሚመለከቱ ተቋማት፤ መንግስት የሚሰራቸውን መልካም ስራዎች ለሕብረተሰቡ የማሳወቅ ስራ ይሰራሉ፡፡ የዴሞክራሲ ተቋማት ደግሞ መንግስት፣ በእቅድ የሚይዛቸው ጉዳዮች፣ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች፣ በሚያወጣቸው መመሪያዎች ደንቦችና አዋጆች ክፍተቶች ካሉ ያንን የመተቸት ስልጣንና ኃላፊነት አለባቸው፡፡ እኛም በድፍረት መንግስትን በመተቸት መንግስትም እጁን ሰብሰብ እንዲያደርግ እና ውሳኔዎችን ዳግም ማየት እንዲችል የተደረገበት ሁኔታ አለ፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ከባለፉት ዓመታት የወሰድናቸው ተሞክሮዎች ናቸው፡፡

በቀጣይም እነዚህን ልምዶች ከማስቀጠል ባሻገር ተቋሙ በአዋጅ የተሰጠውን፤ አስፈፃሚ አካላት የሚያወጧቸው ህጎችና ደንቦች በህገ መንግስቱ ላይ ከተቀመጡ የዜጎች መብቶችን ጋር የማይቃረኑ መሆናቸውን የመመርመር ኃላፊነት በተጠናከረ መልኩ ለመወጣት ራሱን የቻለ ክፍል በማቋቋም ሰፊ ስራ ለመስራት አቅዶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

ከዚህ ቀደም ከዚህ ጋር በተገናኘ በጉምሩክ ኮሚሽን ላይ ምርመራ አድርገናል፡፡ አንድ የጉምሩክ ኃላፊ አንድን የጉምሩክ ሰራተኛ በሙስና ከጠረጠረ ወዲያው ያለ ምንም ማስጠንቀቂያ ከስራ እስከ ማባረር የሚደርስ ስልጣን ይሰጠዋል፡፡ ይህ ተገቢ አይደለም፡፡ ዜጎች የመደመጥ መብት አላቸው፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮችን እንመረምራለን፡፡

የዜጎችን መብት የሚጣረሱ በርካታ የሚወጡ ህጎች አሉ፡፡ ለአብነትም በዚህ ዓመት የምርመራ ስራ ያካሄድንበትን ለመምህራን በሚሰጥ ቤት ላይ የወጣ ሕግን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለመምህራን ቤት የሚያቀርብ መሆኑ ይታወቃል፤ ነገር ግን በዚህ ሕግ መሰረት ቤት የሚሰጣቸው መምህራን ቤቱን የሚወርሱበት ሁኔታ የለም፡፡ ቤቱን የሚጠቀሙም በሕይወት እስካሉ ብቻ ነው። ይህ የዜጎችን ንብረት የማፍራት መብት መገደብ ነው። ስለዚህ ይህንን እና መሰል ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከት የተደራጀ ክፍል የምናቋቁም ይሆናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡-ስሰጡን ማብራሪያ እናመሰግናለን።**

**ዶክተር እንዳስ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# የኢትዮጵያ አየር መንገድ የስኬት ምስጢር

**ሰው መሆን**

ዓለም የተጨነቀችበት ግዜ ነበር። ሰው ሁሉ በሩን ዘግቶ ጎዳናዎች ጭር ብለው የሞት መንፈስ የረበበበት ወቅት። የኮሮና (የኮቪድ 19) ወረርሽኝ ከወደ ቻይና ተነስቶ በመላው ዓለም በመስፋፋቱ ምክንያት የሰው ልጅ ይገባበት ጥግ የሚፈልግበት አስቸጋሪ ወቅት። መንገዶች ተዘግተው፣ መዝናኛ ስፍራዎች በራቸውን ጠርቅመው የመንግስትና የግል ድርጅቶች ሰራተኞቻቸውን ወደ ቤታቸው ሸኝተው እጃቸውን አጣጥፈው የተቀመጡበት አስቸጋሪ ግዜ። በወቅቱ እጅግ ጥቂት የሚባል በጥንቃቄ የተሞላ እንቅስቃሴ ብቻ ይደረግ የነበረበት የፈተና ዘመን።

በዚህ የኮቪድ ዘመን አገራትን ከአንዱ ጫፍ ወደ አንዱ ጥግ በማገናኘት፣ የገቢና የወጪ ንግድን በማቀላጠፍ ወደር የማይገኝላቸው ታላላቅ አየር መንገዶች የእንቅስቃሴ ገደብ ውስጥ ገብተው ወረርሽኙ ካደረሰው የሰው ልጅ ሕልፈትና ማሕበራዊ ቀውስ ባሻገር ከፍተኛ ኪሳራ አስተናገዱ። በወረርሽኙ ምክንያት ለወራት የዓለም አቪዬሽን ኢንዱስትሪ ክፉኛ ተመታ። በእውነቱ በሺዎች የሚቆጠሩ አየር መንገዶች የኢንፌክሽኑን ስርጭት ለመግታት የጉዞ ገደቦችን ሲያስተዋውቁ እና ድንበሮቻቸውን ሲዘጉ በሺዎች የሚቆጠሩ አየር መንገዶች በረራቸውን ለማቆም እና ስራቸውን ለመሰረዝ ተገደዱ።

የእርምጃዎች መጥፎ ውጤት በዋነኝነት የተሰማው ከወረርሽኙ በኋላ ታላላቅ አየር መንገዶች የደረሰባቸውን ጫና ይፋ ሲያደርጉ ነበር። በተለይ አፈጻጸማቸው እያሽቆለቆለ መምጣቱን እና ኪሳራን ለማወጅ መገደዳቸውን ይፋ ያደረጉ በርካቶች ነበሩ። ለምሳሌ ቨርጂን አውስትራሊያ፣ ፍላይቤ እና ኮምፓስ አየር መንገድ ክፉኛ ወድቀዋል፤ የአስተዳደር ጫና ውስጥ ገብተዋል። በተለይ በይፋ ኪሳራ ማወጃቸው ኮቪድ 19 ዓለም አቀፍ ስጋት መሆኑ ካበቃ በኋላ እንኳን መነጋገሪያ ነበር።

በምሳሌነት የጠቀስናቸውና ተጨማሪ በርካቶች በአቪዬሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ የሚሳተፉ አየር መንገዶች በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ሲፍረከረኩ ነበር። ይሁን እንጂ ብርቅዬ የምስራቅ አፍሪካ ፈርጥና የአፍሪካ ኩራት የሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በተቃራኒው ጫናውን ተቋቁሞ “በዚህ ችግር ተጠልፎ ይወድቃል” በማለት የተነበዩለት ብዙሃን አሳፍሮ ግዙፍ ስኬት ማመዝገብ ቻለ። እንደ ታሪክ የምናወራው ይህ ስኬት ከረጅም ዓመታት በፊት የተከሰተ አይደለም። ይህ ታሪክ ከሁለትና ሶስት ዓመታት በፊት የተከሰተ በኢንዱስትሪው ወስጥ ብዙሃንን ያነጋገረና ለኢትዮጵያ አየር መንገድ አድናቆትን ያስገኘ የቅርብ ግዜ ትዝታ ነው።

የአየር መንገዱ ስኬት በዚህ ብቻ የሚገለፅ አይደለም። ለበርካታ አስርት ዓመታት ምቹ አጋጣሚ በነበረበት ወቅት ብቻ ሳይሆን በፈተና ግዜም አውሎ ንፋሱን መቋቋም የጠንካራ ተቋማት መገለጫ እንደሆነ አንዱ ማሳያ መሆን ችሏል። ይህ ስኬቱ ደግሞ በዓለማችን ላይ አሉ ከሚባሉ አየር መንገዶች ውስጥ አንዱ አድርጎታል። ብዙዎች ሊወዳጁት አብረውት ሊሰሩ የሚሹ ናቸው። በየዓመቱ በሚደረጉ የእውቅናና የሽልማት ስነስርዓቶች ላይ የኢትዮጵያ አየር መንገድን አናጣውም። የቅርብ ግዜውን እናንሳ ብንል እንኳን ሁለት ታላላቅ ስኬቶች ማስመዝገቡን እንረዳለን።

የመጀመሪያው ከአውሮፓውያኑ ዘመን አቆጣጠር 2020 ጀምሮ እስካሁን ድረስ “የአፍሪካ ምርጡ አየር መንገድ” የሚል ሽልማትን “Business Traveller Awards” ማግኘቱ ሲሆን ሌላው ደግሞ ከቀናት በፊት የሰማነው ከመጀመሪያዎቹ ዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት ማኅበር /IATA/ የደኅንነት አመራር ቻርተር ፈራሚዎች አንዱ መሆኑን ነው። የደህንነት አመራር ቻርተር ስምንት ዋና ዋና የደኅንነት አመራር መርሆዎችን በመተግበር የደኅንነት ባህል ለማጠናከር ያለመ እንደሆነ የሚታወቅ ነው። እነዚህ ስኬቶች አየር መንገዱ እያስመዘገባቸው ከሚገኙ በርካታ ዓለማቀፍ ድሎች ውስጥ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው።

የአየር መንገዱ በአስቸጋሪ ግዜያቶች ሳይቀር የሚያስመዘግባቸው ስኬቶች ስንመለከትና “ለመሆኑ የስኬት ሚስጥሮቹ ምን ይሆኑ” ብለን መጠየቃችን አይቀርም። በተለይ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ትላልቅ ተቋማት ልክ እንደ አየር መንገዱ የስኬት ማማ ላይ እንዲቀመጡ መሰል የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት በተምሳሌትነት ለመውሰድ ስንሻ ይህንን ጥያቄ ማንሳታችን አይቀርም። ይህ ጥያቄ በእኛ በኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ብዙ የተባለለትና የተመረመረ ጉዳይ ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስኬት በሁለት ምክንያቶች ሊወሰድ እንደሚችል የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ ያምናል። የመጀመሪያው የአየር መንገዱ የጠራ “ራዕይ” እና በመንግስት የእለት ተእለት ስራዎች በሚያከናውንበት ወቅት የሚያገኘው ነፃነት ነው። መረጃዎችን ስንመለከት የኢትዮጵያ አየር መንገድ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር የ2025 ሊያሳካው ያስቀመጠውን ራዕይ በ2018 ላይ እንዳሳካው እንመለከታለን። ከዚያ አልፎ 2025 ሳይደርስ በ2035 ያስቀመጠውን ራዕይ ለማሳካት እቅድ መንደፉን መረጃዎች ያሳዩናል።

አየር መንገዱ በኢትዮጵያ መንግስት ባለቤትነት ቢታወቅም በባለሙያዎች መመራቱ፣ ፍፁም ሙያዊ ስነ ምግባር፣ የአገልግሎት ሰጪነት ስሜት የተላበሱ ሰራተኞች ማካተቱ ለስኬቶቹ ዋና ምንጭ እንደሚሆኑ መገመት አያዳግትም። የአቪዬሽን ንግዱ እንደማንኛውም ኮርፖሬሽን በጥልቅ እንዲመራ የሙያ ነፃነት መኖሩ ለተከታታይ ዓመታት የኢትዮጵያ አየር መንገድ “የአፍሪካ ምርጡ አየር መንገድ” (Best African Airline) የሚል ዘውድ እንዲደፋ ማድረጉ አያጠራጥርም።

ይህ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ ፈተናዎች (የኮቪድ ወረርሽኝ የመሰሉ) በሚመጡበት ወቅት ኪሳራን ማወጅ ሳይሆን ትርፍን ማግኘት እንዲያስችለው አድርጎታል። በርካቶች የአየር መንገዱ ስኬት “በዓለም ላይ ያለው የምጣኔ ሀብት ቀውስ መባባስ፣ የነዳጅ ዋጋ መናር እንዲሁም ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ” ባለበት ወቅት መሆኑ ጥንካሬውን እንደሚያሳይ እንዲመሰክሩለት አስገድዷቸዋል።

ሌላው የኢትዮጵያ አየር መንገድ የስኬት ምንጭ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ይህንን እድል ለመጠቀም የአቪዬሽን የአመራር ጥበብ የሚጠይቅ ቢሆንም እድሉ በራሱ የሚያመጣው ስኬት በቀላሉ የሚታይ አይሆንም። የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ላይ ትኩረታቸውን አድርገው የሚፅፉ ተንታኞች ኢትዮጵያ መካከለኛው ምስራቅን ከአፍሪካ፣ ከእስያና ከአውሮፓ ጋር የምታገናኝ ማእከል እንድትሆን መልከዓ ምድራዊ አቀማመጧ ምቹ አጋጣሚን የሚፈጥር እንደሆነ ይናገራሉ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አዲስ አበባ በርካታ የአቪዬሽን ትራፊክን መሳብ እና ማስተላለፍ የምትችልበት ማዕከል ሆናለች። የአየር መንገዱ ኤክስፐርቶች አመራሮች ይህንን እድል በአግባቡ ለመጠቀም ምክንያት እንደሚሆኑ አያጠራጥርም። በተለይም ከእስያ ወደ አሜሪካ አህጉራት የሚደረጉ በርካታ በረራዎች በዚሁ ትራፊክ ክልል ውስጥ እንደሚደረጉ መረጃዎች ያመለክታሉ።

> **የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስኬት የመሰረተ ልማት ማስፋፊያ እንደሆነ ይነገራል። ባለፉት ሁለትና ሶስት አስርት ዓመታት ውስጥ በመሰረተ ልማት ረገድ በርካታ ለውጦች አስመዝግቧል። የአንድ አየር መንገድ ስኬት በሚያገኘው ትርፍ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በመልሶ ማልማትና ኢንቨስትመንት አማራጭ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስኬት ተጠቃሽ ነው**

ሌላው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስኬት የመሰረተ ልማት ማስፋፊያ እንደሆነ ይነገራል። ባለፉት ሁለትና ሶስት አስርት ዓመታት ውስጥ በመሰረተ ልማት ረገድ በርካታ ለውጦች አስመዝግቧል። የአንድ አየር መንገድ ስኬት በሚያገኘው ትርፍ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በመልሶ ማልማትና ኢንቨስትመንት አማራጭ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስኬት ተጠቃሽ ነው።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በአገር ውስጥ በመሰረተ ልማት ማስፋፊያ ከሚያከናውናቸው ተግባራት ባሻገር በሌሎች አገራት የሚመሩ አየር መንገዶችን ድርሻ በመግዛት የሄደበት ርቀት ዓለም አቀፍ ተፅእኖ ፈጣሪነቱን ከሚያሳዩ ማስረጃዎች መካከል በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት ውስጥ ነው።

አዲስ አበባ በአፍሪካ ትልቁን አየር ማረፊያ ለማልማት እቅድ እንዳላት የቀድሞው የአየር መንገዱ ስራ አስፈፃሚ አቶ ተወልደ ገብረማሪያም ይፋ ማድረጋቸውን እናስታውሳለን። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ይህንን መሰረተ ልማት ለማልማት 5 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ወጪ ለማውጣት ማቀዱን ስንሰማ በመሰረተ ልማት ረገድ ለማምጣት የታሰበውን ለውጥ እና ቁርጠኝነት ያሳየናል። ይህ ፕሮጀክት እውን ሆኖ ቢጠናቀቅ የተጨናነቀ አውሮፕላን ማረፊያ ከማስቀረት ባሻገር ኢትዮጵያ ተመራጭ መዳረሻ እንድትሆን እንደሚያስችላት አያጠራጥርም።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ጥልቅ ስኬት መንግስት ከጣልቃ ገብነት የፀዳ ጥበቃ በማድረጉ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ መታመን ይኖርበታል። ይህ አካሄድ ተገቢና ቀጣይነት ሊኖረውም ይገባል። በተለይ ሙያዊ ነፃነት እንዲኖረው፣ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነቱ እንዲጨምር እንዲሁም በማንኛውም ሁኔታ ድጋፍ ሲያስፈልገው እንዲያገኝ በመንግስት በኩል የሚደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

መንግስት ከስራቸው መራቅ ባለመቻሉ የሞቱት አየር መንገዶች በርካታ ናቸው። በምሳሌነት ናይጄሪያ ኤርዌይስ ሊሚትድ፣ ኤር አፍሪካን፣ ጋና ኤርዌይስ፣ ጋምቢያ አየር መንገድ፣ ኤር አንጎላ፣ ቦትስዋና አየር መንገድ፣ ኮንጎ አየር መንገድ፣ ኤር ጅቡቲ እና ሌሎችም መጥቀስ ይቻላል። ይህ የሚያመላክተን የፖለቲካና የመንግስት አላግባብ እጅ መርዘም የአቪዬሽን ኢንዱስትሪው ስኬት ጋሬጣ እንደሚሆን ነው። የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን መገንዘቡ የምስራቅ አፍሪካ ፈርጥ፣ የአፍሪካ ኩራት የሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ እንዲፈጠር እድል ሆኗል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የኢትዮጵያ አየር መንገድ እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር በታህሳስ 21 ቀን 1945 የተመሰረተ ሲሆን ሚያዝያ 8 ቀን 1946 ስራ ጀምሯል። ከጅምሩ ጀምሮ ስኬታማ ለመሆን እና በአፍሪካ አውራ አየር መንገድ ለመሆን ያስቻሉት በርካታ ስራዎች አከናውኗል። ከላይ ካነሳናቸው ምስጢሮች ባሻገር የጥገና መሰረተ ልማቱን ማዳበር፣ የአብራሪዎች፣ የመሀንዲሶች እና የካቢን ሰራተኞች አጠቃላይ ስልጠና መስጠት መቻሉ የስኬቶቹ ምንጭ ነው። በዚህ ምክንያት በአህጉሪቱ ከመጀመሪያዎቹ አየር መንገዶች እና አንጋፋና ስኬታማ ያደርገዋል። ለዚህ ነው ይህንን አየር መንገድ ማንኛውንም ዋጋ ከፍለን ልንጠብቀው፣ ልናሳድገውና የኢትዮጵያውያን የኩራት ምንጭ ልናደርገው የሚገባው። ሰላም !

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# ኢትዮጵያን በቡና ከማስተዋወቅ ባለፈ የቡና ቱሪዝም መዳረሻ ማድረግን ያለመው መድረክ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ምርትና አገልግሎትን ለማስተዋወቅ እንዲሁም ጠንካራ የገበያ ትስስር ለመፍጠር ኤግዚቢሽኖችና ባዛሮች ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡ በተለይም ዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች አገርን ከማስተዋወቅ ባለፈ የገበያ ትስሰር በመፍጠር፣ የልምድ ልውውጥና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ጉልህ አበርክቶ እንዳላቸው ይታመናል፡፡ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች በተለያዩ ጊዜያት ሲካሄዱ መመልከት መቻላችንም በዚሁ ምክንያት ነው። ከሰሞኑም በአይነቱ ለየት ያለና በአፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄድ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ መረጃዎች አመልክተዋል፡፡

በአፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄደው ይህ <<ውሜን ኢን ኮፊ>>/ሴቶች በቡናው ዘርፍ ሊባል ይችላል/ የተሰኘው ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ፣ እ.ኤ.አ ከመጪው ጥቅምት 16 እስከ 22 ቀን 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ይካሄዳል፡፡ ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንሱ የ‹‹ውሜን ኢን ኮፊ›› ኢትዮጵያ ማሕበር እና የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን በጋራ የሚያዘጋጁት ነው፡፡

ማሕበሩ በቡና አምራችነትና በቡና የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ተዋናይ የሆኑ ሴቶችን በማደራጀት ከዘርፉ ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ የሚሠራ ማሕበር ነው፡፡ ማሕበሩ ከመንግሥትና ከሌሎች አቻ አካላት እንዲሁም በአገር ውስጥና በውጭ አገር ከሚገኙ ማሕበራት ጋር ተባብሮ ለመሥራት የተቋቋመ ሲሆን፤ ከተመሰረተበት 2009 ዓ.ም ጀምሮ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ በቡና ልማትና ግብይት ዘርፍ ለተሰማሩ ሴቶች ድጋፍና እገዛዎችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በተለይም በቡና ሥራ የተሰማሩ ሴቶች በተለያዩ ዓለም አገራት ተዘዋውረው ዓለም አቀፍ በሆኑ ኤግዚቢሽኖችና ኮንፍረንሶች ተሳትፈው የኢትዮጵያን ቡና መሸጥና ማስተዋወቅ የሚችሉበትን ዕድል በመፍጠር ሰርቷል፡፡

በአሁኑ ወቅትም በአፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄደውን ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ በኢትዮጵያ ለማካሄድ ዝግጅቱን አጠናቋል፡፡ የዚሁ የቡና የኤግዚቢሽንና ኮንፍረንሱ ዋና ዓላማ ምንድ ነው? ምን አስተዋጽኦ ያበረክታል? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ከውሜን ኢን ኮፊ ኢትዮጵያ የቦርድ ሰብሳቢ ወይዘሮ ሳራ ይርጋ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንሱ የኢትዮጵያ ቡና ከምርቱ ጀምሮ እስከ ሲኒ ድረስ ያለው ሂደት የሚተዋወቅበትና ቡና ለኢትዮጵያውያን ምን ማለት እንደሆነ ማሳያት ያስችላል፡፡ በወቅቱ በሚፈለገው ግብይት የገበያ ትስስር መፍጠር፣ የልምድና የዕውቀት ሽግግር ማድረግና ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ብቻ ሳትሆን የቡና ቱሪዝም መዳረሻ ጭምር መሆኗን ማሳየት ደግሞ ሌላው የኤግዚቢሽንና ኮንፈረንሱ ዋና ዓላማ ነው፡፡

በኤግዚቢሽንና ኮንፍረንሱ በዓለም አቀፍ ደረጃ በቡና እሴት መጨመር ላይ የተሰማሩ ሴቶች እንደሚሳተፉ ወይዘሮ ሳራ አስታውቀዋል። በኢግዚቢሽንና ኮንፍረንሱ የአንድ ሳምንት ቆይታ ኮንቬንሽን፣ ኤክስፖና ኦሪጅን ትሪፕ እንደሚከናወን አመላክተው፡፡ በዚህም የኢትዮጵያ ቡና ከመነሻው ጀምሮ በማስተዋወቅና የገበያ ትስስር በመፍጠር በተለያዩ የአገሪቱ ቦታዎች የሚገኙ ቡና አብቃይ አካባቢዎች እንደሚጎበኙ ጠቁመዋል፡፡

ወይዘሮ ሳራ እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያ ቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ ዋና ዓላማ የቡና መገኛ የሆነችው ኢትዮጵያ የቡና ቱሪዝም መዳረሻ እንድትሆን በማድረግ ዓለም አቀፍ ገበያውን በማስፋት የኢትዮጵያን ቡና ማስተዋወቅ ይሆናል፡፡ በዘርፉ የተሰማሩ ሴት ቡና አምራቾች፣ ነጋዴዎችና ላኪዎች በተለያዩ አገራት እየሄዱ የኢትዮጵያን ቡና እያስተዋወቁ ሲሸጡ የኖሩት ብዙ ዋጋ እየከፈሉ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ሁነቶች ከአፍሪካ ውጭ በሆኑ አገራት የሚዘጋጁ በመሆናቸውም በዘርፉ የተሰማሩ ሴቶች ለከፍተኛ ወጪ ይዳረጋሉ፡፡

ይህንን በመረዳት መሰል ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ የቡና መገኛ አገር በሆነችው ኢትዮጵያ እንዲካሄድ ማህበሩ ጥያቄ ማቅረቡን ነው ወይዘሮ ሳራ ያስታወሱት፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ መሰል ኤግዚቢሽኖችና ኮንፍረንሶች በየሁለት ዓመቱ በደቡብ አሜሪካ፣ በማዕከላዊ አሜሪካና አሜሪካ ላይ የሚካሄዱ ቢሆንም፣ በአፍሪካ አገራት ተካሂዶ አያውቅም፡፡ በዚህ መነሻነት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት በማግኘቱ በአፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ላይ ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ ለማካሄድ ዝግጅቱ ተጠናቅቋል፡፡

አፍሪካ ላይ ከላቲን አሜሪካ ያልተናነሰ ቡና አብቃይ አገራት ስለመኖራቸው የጠቀሱት ወይዘሮ ሳራ፤ በአሁኑ ወቅት በአፍሪካ መዲናዋ አዲስ አበባ ከተማ ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ ለመጀመሪያ ጊዜ ለማካሄድ ዝግጅቱ መጠናቀቁን ነው የተናገሩት፡፡ ይሁንና ብዙዎች በአፍሪካ አገር ላይ እንዲህ አይነት ሁነት ማዘጋጀት ይቻላል የሚል እምነት እንዳልነበራቸው አስታውሰው፤ እኤአ በ2021 በአፍሪካ መዲና አዲስ አበባ ከተማ ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ እንዲዘጋጅ ፈቃድ ማግኘት እንደቻሉና ከአንድ ዓመት በላይ የቅድመ ዝግጅት ሥራ ሲሰራ መቆየቱን አስታውቀዋል፡፡

ወይዘሮ ሳራ እንዳሉት፤ ውሜን ኢን ኮፊ ኢትዮጵያ ማህበር ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመሆን ይህን ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ ለማዘጋጀት በርካታ ሥራዎች ሲሠራ ቆይቷል፡፡ የዝግጅት ሥራው ከአንድ ዓመት በላይ ጊዜ ወስዷል፤ በርካታ በቡና ልማትና ግብይት ዘርፍ የተሰማሩ ሴቶች ከፍተኛ ተሳትፎ አድርገውበታል፡፡ ከማህበሩ ሴት አባላት በተጨማሪ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የፋይናንስ ተቋማትና ሌሎች የተለያዩ አጋር አካላት ጭምር ባደረጉት ድጋፍ ዝግጅቱ ተጠናቅቆ ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንሱ ሊካሄድ ጥቂት ቀናት ብቻ የቀሩት ሲሆን፣ እንግዶች እየተጠባበቁ ይገኛሉ፡፡

ይህ ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ በዋናነት ዓላማ አድርጎ የተነሳው ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ብቻ ሳትሆን የቡና ቱሪዝም መዳረሻ አገር መሆኗን ማስተዋወቅ ነው የሚሉት የቦርድ ሰብሳቢዋ፤ ሰዎች እንደ መካና እየሩሳሌም ኢትዮጵያን ለቡና ብለው ማየት እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡ ይህን ማድረግ ሲቻል የሚገኘው ውጤት እጥፍ ድርብ እንደሆነና በዘርፉ ትርጉም ያለው ውጤት ማምጣት እንደሚቻል አመልክተዋል፡፡ ከቡና የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ በተለያየ መንገድ ማሳደግ እንደሚቻል ጠቅሰው፣ በኤክስፖርት ከሚገኘው ገቢ በተጨማሪ ጎዥዎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በሚፈጥሩት የገበያ ትስስርና ግዢ ገቢ እንደሚገኝም ተናግረዋል፡፡ እንግዶቹ በሚኖራቸው ቆይታም ገቢ እንደሚገኝ ነው ያመለከቱት፡፡

‹‹ቡና ትልቅ የቱሪዝም አቅም መሆን ይችላል›› ያሉት ወይዘሮ ሳራ፤ በዚህ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስም ከተለያዩ የዓለም አገራት የሚመጡ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ስለመኖራቸው ተናግረዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ ለእነዚህ እንግዶች ቡና ከምርቱ ጀምሮ እስከ ስኒ ድረስ ያለውን ሂደት ለማሳየት ዝግጅት ተደርጓል፡፡ ለዚህም አራት ቦታዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ አንደኛው ጉጂ ዞን ሀምበላ ላይ የሚገኝ የቡና ሎጅ ሲሆን፣ በእዚህ ቦታ ላይ ከቡና እርሻ በተጨማሪ የቡና ቅምሻም ይካሄዳል። ሌላው በንሳ ላይ የሚገኝ ሎጅ አርደንት ኮፊ ሲሆን፤ እሱም እንዲሁ የቡና እርሻና የቡና ማቀነባባሪያ ያለው ነው፡፡ ከፋ ላይ የሚገኙት ደሀብ ቡና እና ጋላኒ ቡናም እንዲሁ ትልቅ የቡና እርሻ ያላቸውና ቡና የማምረትና የማቀነባበር ሥራ የሚሠራባቸውና የሚጎበኙ ቦታዎች ናቸው፡፡

በዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንሱ ላይ የሚሳተፉ እንግዶች በእነዚህ አራት ሳይቶች በሚያደርጉት ጉብኝት የኢትዮጵያን ቡና ከምርት ጀምሮ የማወቅና የመረዳት አጋጣሚን ይፈጥርላቸዋል። ይህም የገበያ ትስስር ለመፍጠር በር የሚከፍት በመሆኑ ‹‹በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ›› እንደሚባለው ከሚፈጠረው የገበያ ዕድል በተጨማሪ የኢትዮጵያ ቡናን ማወቅና መረዳት ይችላሉ፡፡ በተያያዘም ቡና ማለት ለኢትዮጵያውያን ምን ማለት እንደሆነና የሕይወት ዘይቤያቸው መሆኑን ጭምር በመረዳት የኢትዮጵያን ቡና በብዙ የሚተዋወቁበት ሰፊ ዕድል የሚፈጠርበት አጋጣሚ ይሆናል፡፡ በዚህም ሴቶች ትልቅ አበርክቶ አላቸው፡፡



ወ/ሮ ሣራ ይርጋ

ወይዘሮ ሳራ ጥናቶች ዋቢ አድርገው እንዳሉት፤ በአገሪቱ 70 በመቶ ያህሉ የግብርና ሥራዎች የሚሰሩት በሴቶች ነው፡፡ ከግብርና ሥራዎች አንዱ የሆነው የቡና ሥራም በአብዛኛው በሴቶች የሚሰራ ነው፡፡

በውሜን ኢን ኮፊ ኢትዮጵያ ማሕበር አባል መሆን የሚችሉት በቡና ሥራ ውስጥ የተሰማሩ ሴቶች ስለመሆናቸው ገልጸው፤ እነሱም ቡና አምራቾች፣ ቡና ቆይዎች፣ ቡና አቀነባባሪዎች፣ ላኪዎችና ቀማሾች መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡ ማህበሩ በቡና አምራችነት የተሰማሩ ሁለት ቡና አምራች ሕብረት ሥራ ማሕበራትን ጨምሮ በድምሩ 70 የሚደርሱ አባላት እንዳሉትም ጠቁመዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አሸት ቡና የሚደርስበት ወቅት እንደሆነ ያነሱት ወይዘሮ ሳራ፤ ጊዜው በእጅጉ ተመራጭ እንደሆነና እንግዶቹ የተንዠረገገውን የቡና ፍሬ በእርሻ ቦታ ላይ ማየት እንደሚያስችላቸውም ጠቁመዋል፡፡ ይህም የኢትዮጵያን ቡና ከመነሻው ጀምሮ ያለውን ሂደት አውቀውና ተረድተው እንዲገዙ እንደሚያስችል አመልክተዋል፡፡

የቦርድ ሰብሳቢዋ እንዳብራሩት፤ በአፍሪካ የመጀመሪያ በሆነው ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፈረንስ ላይ በቡና ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላት በሙሉ ይሳተፋሉ፡፡ ተሳታፊዎቹ በአጠቃላይ ከ50 የተለያዩ ዓለም አገራት ይመጣሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ቢያንስ ከ33 አገራት ሁለት ሁለት ኃላፊዎችና አባላት ይገኛሉ። በዚህም መድረኩ ቡናውን ከማስተዋወቅ ባለፈ የገበያ ትስስር የሚፈጠርበት እንደመሆኑ በሚኖረው የአንድ ሳምንት ቆይታ በአንደኛው ቀን በሚኖረው መርሃ ግብር ሰፊ የገበያ ትስስር የሚፈጠር ይሆናል፡፡

በርካታ የዓለም አገራት የኢትዮጵያን ቡና እንደሚፈልጉትና እንደሚጠቀሙበት የጠቀሱት ወይዘሮ ሳራ፤ የዓለም አገራት የኢትዮጵያን ቡና ፈልገው መምጣት እንዲችሉ መሥራት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ በተለይም ሴቶች በቡና ምርትና ማቀነባበር እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች መሥራታቸው የሚኖረው አበርክቶ ትልቅ መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ በቡና ሥራ የተሰማሩ ሴቶች ከኢኮኖሚው በተጨማሪ ማሕበራዊ ግንኙነቶችን የሚያጠናክሩበት በመሆኑ በቡና ሥራ ሴቶች ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡ ለዚህም ውሜን ኢን ኮፊ ኢትዮጵያ ማህበር በአፍሪካ የመጀመሪያ የሆነውን ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ በማዘጋጀት ኢትዮጵያ የቡና መገኛ አገር ብቻ ሳትሆን የቡና ቱሪዝም መዳረሻ ጭምር መሆኗን ያስተዋውቃል፡፡

ከ75 በላይ ግለሰብ አባላት እና ከ200 በላይ በቡና አብቃይ አካባቢ የተደራጁ ቡና አምራች ሴቶች አባላት ያሉት ውሜን ኢን ኮፊ ኢትዮጵያ ማህበር፤ በተጨማሪም በተለያዩ የአገሪቱ ቡና አብቃይ ክልሎች የሚገኙ በችግኝ ማፍላት፤ መሬት ማዘጋጀት፤ መትከል፤ መንከባከብ፤ ብሎም ፍሬውን በመሰብሰብ፤ በማዘጋጀትና ወደ ገበያ በማቅረብ፤ በማማከርና ስልጠና በመስጠት እንዲሁም አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማሩ ሴቶችንም አካትቷል፡፡

ማህበሩ አባላቱን በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቁና ተወዳዳሪ ለማድረግ አቅዶ እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ ሲሆን፤ እቅዱን ዳር ለማድረስ በሚያደርገው ጥረት በአገር ውስጥ እና በውጭ ከሚገኙ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሠራል፡፡ ማህበሩ እኤአ ከሚያዚያ 2017 ጀምሮ የኢንተርናሽናል ውሜን ኢን ኮፊ አሊያንስ (IWCA) ቻፕተር አባልም ነው።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ትኩረት ያጡት የሙያ ትምህርቶች

ዋስልኝ አየለ

የመስከረም ወር የትምህርት መጀመሪያ ወር ነውና ትምህርታዊ አጀንዳዎች ይበዛሉ፡፡ በተለይም በዚህ ዓመት ደግሞ የተለመደው የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ እንዲሁም የቅድመ ምረቃ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ብቻ አይደለም አጀንዳ የሆነው። የድህረ ምረቃ ትምህርትም በዚህ ዓመት የመስከረም ወር አጀንዳ ሆኗል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው የትምህርት መመሪያ መሰረት የድህረ ምረቃ ትምህርት በብሔራዊ ፈተና መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ዩኒቨርሲቲዎች በራሳቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየፈተኑ ያስተምሩ የነበረበት አሰራር ከዚህ ዓመት ጀምሮ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ሆኗል፡፡ ከፊታችን ሰኞ መስከረም 28 ቀን እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም ይሰጣል፡፡

በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን አንድ ልብ ያልተባለ ነገር አለ፡፡ ይሄውም የሙያ ትምህርት ነው፡፡ የሙያ ስል የተለመዱትን የሕክምና፣ የምህንድስና.... አይነት ትልቅ ትኩረት የተሰጣቸውን ማለቴ አይደለም፡፡ የእጅ ሙያ ትምህርት የሆኑት ናቸው ትኩረት ያልተሰጣቸው፡፡ በተለምዶ ቴክኒክና ሙያ እየተባሉ የሚጠሩት ማለት ነው፡፡ ቴክኒክና ሙያ ውስጥ አሉ የሚባሉት ራሱ አገር በቀል የሆኑ የእጅ ሙያ ትምህርቶች ትኩረት የተሰጡበት አይመስልም፡፡ ምክንያቱም የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ክፍሎች ውስጥ የሸክላ ሥራ፣ የቤት ውስጥ ቁሳቁስ ሥራ፣ የባህላዊ መሳሪያዎች አሰራር የመሳሰሉት ሲወራባቸው አይሰማም፡፡

የአንዲት አገር የሥልጣኔ እና የዕድገት መገለጫ ኢንዱስትሪ ሆኗል፡፡ የትልልቅ ኢንዱስትሪዎች መነሻ ደግሞ የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡ የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ደግሞ እነዚህ አገር በቀል የሆኑ የማህበረሰቡ የእጅ ሥራዎች ናቸው። እነዚህ አገር በቀል የጥበብ ሥራዎች በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ደረጃ ትኩረት ቢሰጣቸው ወደ ዘመናዊነት ያድጋሉ። ፈጠራ ፈጠራን እየወለደ ዘመናዊ ኢንዱስትሪ ይሆናሉ።

ሰዎች ለሥራ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ሲሄዱ፤ ከሄዱበት አካባቢ ያለ ባህላዊ የመገልገያ ዕቃ ይገዛሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከዘመናዊ የፋብሪካ ዕቃዎች በተሻለ የሚወደዱ እና የሚፈለጉ ባህላዊ ዕቃዎች አሉ። እነዚህ ዕቃዎች የተሰሩት ከዋናው ጥሬ ዕቃ በባህላዊ መንገድ ነው፡፡ እነዚያን ዕቃዎች የሰሩ ሰዎች ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ አይደሉም። በልማዳዊ መንገድ ነው የሰሩት፡፡ የሰሩት ሰዎችም እንደ ባለሙያ ሳይሆን የሚታዩት እንደ ኋላቀር ነው፡፡ ከእነዚያ ባለሙያዎች ይልቅ ለአገር ምንም ጠብ ያላደረገ ዲግሪ የደራረበ ሰው ይከበራል፡፡

እውነታው ግን በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ «የተማረ» ከሚባለው ዜጋ ይልቅ ዘመናዊ ትምህርት ያልተማረው ለኢንዱስትሪ ግብዓቶች ይቀርባል፡፡ ለምሳሌ፤ የግብርና መገልገያ ዕቃዎች አሁንም በባህላዊ መንገድ የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ የተማረ የሚባለው ግን ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎችን መገጣጠም አልቻለም። እነዚያው ጥቂቶችም ቢሆን ከውጭ የሚመጡ ናቸው፤ ለዚያውም በብዛት የሉም፡፡

ለመስክ ሥራ በምንሄድባቸው የገጠር አካባቢዎች ብዙ የዕደ ጥበብ ሥራዎች ይገኛሉ። የተማረ የሚባለው የሕብረተሰብ ክፍል እነዚህን ዕቃዎች ይገዛል፤ እሱ ግን የመገልገያ ዕቃዎችን በዘመናዊ መንገድ ማምረት የሚያስችል ክሕሎት የለውም። የኤሌክትሮኒክስ ዕቃ ብቻ ሳይሆን የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች ሁሉ ከውጭ የሚመጡ ናቸው፡፡ መዘመን እና መሰልጠን የተባለው እነዚህን የፈረንጅ ምርቶች መግዛት ነው። በአንፃሩ በአገር በቀል ጥበብ የተሰሩት ዕቃዎች የኋላቀርነት መገለጫ ተደርገው ይታያሉ፡፡

እርግጥ ነው አንዳንድ ባሕላዊ ዕቃዎች በጥንካሬም ሆነ በአገልግሎት ፍጥነት ከፈረንጅ ምርቶች ያነሱ ናቸው፡፡ ዳሩ ግን በሥርዓተ ትምህርታችን ውስጥ ተካተው ትኩረት ቢሰጣቸው የመዘን ዕድል ይኖራቸዋል፡፡ የእጅ ሙያ ትኩረት ቢሰጠው በራሱ እየዳበረ ይሄድ ነበር፡፡ ባሕላዊ ዕቃዎችን የሚሰሩት ሰዎች ራሱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻሉት ይሄዳሉ፡፡ ስለዚህ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና ትኩረት የሚሰጠው ቢሆን ይዳብር ነበር ማለት ነው፡፡

ቀደም ሲል በነበሩት ጊዜያት «የእጅ ሥራ» የሚባል የትምህርት አይነት ነበር፡፡ ቢሆንም ግን በቂ ትኩረት የተሰጠው አልነበረም፤ የንድፈ ሀሳብ ትምህርት የለውም። ተማሪዎች የሚችሉትን የእጅ ሥራ ይዘው እንዲመጡ ይደረጋል፡፡ አንዳንዱ የግብርና መሳሪያዎችን ይሰራል፣ አንዳንዱ የጦር መሳሪያ ይሰራል፣ አንዳንዱ የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ይሰራል፡፡ የመጨረሻ ግቡ ግን የቁጥር ነጥብ ለማግኘት ብቻ ነው፡፡ ተማሪው በዚያ ሙያ የመቀጠል ፍላጎት የለውም፤ ምክንያቱም ያ ሙያ እንደ ትልቅ ሙያ የሚቆጠር አልነበረም፡፡ ይህ ችግር እነሆ አሁን ድረስ ስለዘለቀ አሁንም የእጅ ሙያ በትምህርት ውስጥ ትኩረት ሲሰጠው አይታይም፡፡

ከሁለት ዓመት በፊት ይመስለኛል የኦሮሚያ ክልል መንግሥት በቡራዩ አካባቢ የእጅ ሙያ ትምህርት ቤት አስገንብቶ ሲያስመርቅ አጀንዳ ሆኖ እንደነበር አስታውሳለሁ። በወቅቱ ብዙ ሰዎች አድንቀዋል፡፡ ምክንያቱም የዘመናዊ ኢንዱስትሪ መነሻው የአካባቢ የእጅ ሙያዎችን ማዳበር ነው፡፡ ይህ የኦሮሚያ ክልል ጅማሮ ግን በአገር አቀፍ ደረጃ አጀንዳ ሲሆን አላየንም። አሁንም ትምህርት ሲባል ያው የተለመደው የአውሮፓ ሳይንቲስቶችን ስም እና ንድፈ ሀሳብ መሸምደድ ነው ትኩረት የሚሰጠው። ጎበዝ ተማሪ የሚባለውም ያንን ሸምድዶ ከፍተኛ ቁጥር ሲያስመዘግብ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ከሚታዩ የጎበዝ ልጆች የፈጠራ ሥራዎች በስተቀር ተግባር ተኮር ውጤት አልታየም፡፡

ይባስ ብሎ እንዲያውም የእጅ ሙያ ያላቸው ልጆች እንደ ሰነፍ የሚታዩበት አጋጣሚም አለ፡፡ የተለመደው ጎበዝ ተማሪ ማለት ኬሚስትሪ፣ ፊዚክስ፣ ባዮሎጂ፣ ታሪክ፣ ጂኦግራፊ.... ሸምድዶ ከፍተኛ ቁጥር የሚያመጣ ነው፡፡ የፊዚክስ ውጤት የሆነውን አንድ ቀላል ማሽን ከመሥራት ይልቅ የፊዚክስ ንድፈ ሀሳብ ሸምድዶ ከፍተኛ ቁጥር ማምጣት የተሻለ ጎበዝ ተማሪ ያሰኛል፡፡ ከዚህ ልማድ መላቀቅ አለብን፡፡

ይህ ይሆን ዘንድ ለእጅ ሙያ ጥበቦች ትኩረት መስጠት አለበት፡፡ እንደ ትምህርት ሊታዩ ይገባል፤ እንደ ሳይንሳዊ ፈጠራ ሊታዩ ይገባል፡፡ ቀላል ማሽኖች እንደ ኢንዱስትሪ መነሻ መታየት አለባቸው። በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ መካተት አለባቸው። በልማዳዊ መንገድ የሚሰሩ የአካባቢ ሰዎች ልክ እንደ ፊዚክስ መምህር መማሪያ ክፍል ውስጥ ገብተው ልምዳቸው ማካፈል አለባቸው፡፡ የመማሪያ መጻሕፍት ላይ ምሳሌ የሚሰጠው በአካባቢ ያሉ ነገሮችን ነው፡፡ ስለዚህ እነዚያን ነገሮች በተግባር የሚሰሩ ሰዎች ልምድ ቢያካፍሉ፣ ትምህርት ቢሰጡ ምን ችግር አለው?

የእጅ ሙያ ያላቸው ተማሪዎች ልክ ከፍተኛ ቁጥር አምጥቶ እንደሚሸለመው ተማሪ መሸለምና መበረታታት አለባቸው፡፡ ያኔ ሙያውም ክብር ያገኛል፤ ሥራውን የሚለማመዱ ተማሪዎችም ይፈጠራሉ፡፡ ፊዚክስ 100 ካመጣ ተማሪ ይልቅ አንድ ቀላል ማሽን የሰራ ተማሪ ለፊዚክስ ትምህርት ይቀርባል ማለት ነው፡፡ የእጅ ሙያ ውጤቶች የሳይንስ መነሻ ናቸውና ትኩረት ይሰጣቸው !

# ዓለም አቀፍ

## ኬንያ በሔይቲ ሥርዓተ አልበኝነትን ለመቆጣጠር ፖሊሶቿን ልታሰማራ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

ኬንያ በካሪቢያኗ አገር ሔይቲ ያለውን ሥርዓተ አልበኝነት ለመቆጣጠር ፖሊሶቿን ለማሰማራት ያቀረበችው ጥያቄ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ፈቃድ አገኘ።

የሔይቲ ጠቅላይ ሚኒስትር በተደራጁ ወንጀሎች አገራቸው እየተናወጠች በመሆኗ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ድጋፍ እንዲያደርግ በጠየቁት መሰረት ኬንያ ዓለም አቀፍ የደኅንነት ኃይል ለመምራት ጥያቄ አቅርባ ነበር።

ሔይቲ ለበርካታ ዓመታት በተደራጁ ወሮበላ ቡድኖች ሁከት ስትፈተን ብትቆይም የአገሪቷ ፕሬዚዳንት ጆቬኔል ሞይስ ከተገደሉ ከሁለት ዓመታት በኋላ ከቁጥጥሯ ውጭ ሆኗል።

እነዚህ ቡድኖች ሰፊውን የአገሪቱን ክፍል በመቆጣጠር በነዋሪዎች ላይ ሽብር እየፈጠሩ ነው። እንዲሁም በመቶዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎችንም ገድለዋል ተብሏል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ ወሮበሎችን ትጥቅ ለማስፈታት እና ሥርዓቱንም ወደነበረበት ለመመለስ ጠንካራ የኃይል ርምጃ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት በሔይቲ የሚሰማራውን የኃይል ተልዕኮ ለአንድ ዓመት ያጸደቀ ሲሆን ከዘጠኝ ወራት በኋላም ይገመገማል።

በሔይቲ የሚሰማራው ኃይል የጋራ የደኅንነት ሥራዎችን ያከናውናል። ከሔይቲ ፖሊስ ጋር በመቀናጀት በቁጥጥር ሥር የሚውሉ አካላትንም ለማሰር ሥልጣን ተሰጥቶታል።

በዚህም አገሪቷ ምርጫ ለማካሄድ ሁኔታዎችን ያመቻችላታል። ሔይቲ ከአውሮፓውያኑ 2016 ጀምሮ ምርጫ አላደረገችም። የሔይቲ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዣን ቪክቶር ጄነስ ውሳኔውን “ለረጅም ጊዜ በስቃይ ለነበሩ ሰዎች የተስፋ ጭላንጭል የፈነጠቀ” ሲሉም ጠርተውታል።

ኬንያ በዚህ ተልዕኮ አንድ ሺህ ፖሊሶችን በሔይቲ እንደምታሰማራ ተናግራለች። ለመጀመሪያ ጊዜ ሃሳቡ በቀረበበት ከጥቂት ወራት በፊት የኬንያ ባለስልጣናት የሚያሰማሯቸው ፖሊሶች የመንግሥት ሕንጻዎችን እና መሰረተ ልማቶችን ይጠብቃሉ ብለው ነበር።




ነገር ግን ኬንያ ሁኔታውን ለመገምገም አጣሪ ልዑካንን ከላከች በኋላ እቅዱ ተቀይሯል። ኬንያ በሔይቲ የምታሰማራቸው ፖሊሶች የተደራጁ ቡድኖችን ትጥቅ የሚያስፈቱ፣ ሰላማዊ ዜጎችን የሚጠብቅ እንዲሁም በአገሪቱ ሰላም፣ ደኅንነት እና ጸጥታን በማምጣቱ ረገድ ሚና የሚጫወቱ ይሆናሉ።

የኬንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አልፍሬድ ሙቱዋ ለቢቢሲ እንደተናገሩት አገራቸው ሔይቲ ጠቃሚ መሰረተ ልማቶችን መልሳ እንድትገነባ እንዲሁም የተረጋጋ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት እንድትመሰርት ማገዝ ትፈልጋለች።

## በፓኪስታን የሰው ኩላሊት ለሽያጭ ያዋሉ አዘዋዋሪዎች ተያዙ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በሰሜናዊ ምስራቅ ፓኪስታን በመቶዎች የሚቆጠሩ የሰው ኩላሊቶችን ለሽያጭ አውለዋል የተባሉ የሰውነት አካል አዘዋዋሪዎች በቁጥጥር ሥር ዋሉ።

በቁጥጥር ሥር የዋሉት የሰውነት አካል አዘዋዋሪዎች ስምንት መሆናቸውን ፖሊስ አስታውቋል። የዚህ እንቅስቃሴ መሪ ዶክተር ፋዋድ ሙክታር ከ300 በላይ ኩላሊቶችን ከህመምተኞች በማውጣት ለሃብታም ደንበኞች በመሸጥ ንቅለ ተከላ አድርጓል በሚልም ተከሷል።

ዶክተሩ ከዚህ ቀደም ከፈጸማቸው የሕክምና ስህተቶች ጋር በተያያዘ አምስት ጊዜ በቁጥጥ ሥር ውሎ ነበር። በእነዚህ ወቅቶችም የዋስትና መብቱን ማስከበር ችሏል። የአካል ክፍሎቻቸውን በማስወጣት ሂደቱም ሦስት ሰዎች መሞታቸውን ባለስልጣናቱ ተናግረዋል።

ቡድኑ በምስራቃዊ ፑንጃብ ግዛትና ፓኪስታን በምታስተዳድራት ካሽሚር ውስጥ እንደሚንቀሳቀስ ይታመናል። ንቅለ ተከላዎቹ የተከናወኑት ህመምተኞቹ በማያውቁበትና በመኖሪያ ቤት ውስጥ መሆኑን የፑንጃብ ግዛት አስተዳዳሪ ሞህሲን ናቅቪ ተናግረዋል።

ዶክተሩ ቀዶ ሕክምናውን በሚያደርግበት ወቅት ረዳቱ ሆኖ ሲያገለግል የነበረው አንድ የመኪና መካኒክ መሆኑን አስተዳዳሪው ተናግረዋል።

መካኒኩ ተጋላጭ የሆኑናና አቅመ ደካሞችን ከሆስፒታሎች በማታለልም ወደ መኖሪያ ቤቱ አምጥቷቸዋል ተብሏል። እያንዳንዱ ኩላሊትም እስከ 10 ሚሊዮን ሩፒ (120 ሺህ ዶላር) መሸጣቸውንም አስረድተዋል።

“እኛ ጋር የደረሱት እውነታዎች እና አሃዞች ልብን የሚያሸብሩ ናቸው” ሲሉም ናቅቪ እሁድ በነበረ ጋዜጣዊ መግለጫ ተናግረዋል።

“በርካታ የንቅለ ተከላዎች እና ሕገወጥ ቀዶ ሕክምናዎች ይደረጋሉ። በአሁኑ ወቅት የደረስንባቸው እነዚህን ነው” ብለዋል።

በፓኪስታን የሰዎች የአካል ክፍሎችን ለንግድ ማዋል ሕገወጥ የተደረገው በአውሮፓውያኑ 2010 ነበር። የሰዎች አካላትን ሲሸጡ የተገኙ ሰዎችም ረዘም ያለ እስራት እና ከፍተኛ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣሉ።

ይህም ለውጭ አገር ደንበኞች ሽያጭ እንዲውል የሚበዘብዙ ዶክተሮች፣ ደላላዎችና አሻሻጮች ተግባርን



ያስቆመዋል በሚል ያለመ ነው።

በጥር ወር የፑንጃብ ፖሊስ ጠፍቶ የነበረ የ14 ዓመት ልጅ ኩላሊቱ ተወስዶ አስከሬኑ በመሬት ውስጥ በሚገኝ ቤተሙከራ አግኝቷል። በዚህም አካባቢ ይንቀሳቀስ የነበረ የሰውነት አካል አዘዋዋሪዎች ቡድን እንዳለም ይፋ አድርጓል።

# የሀገር ፍቅር በጥላሁን ገሰሰ አንደበት

**ፅጌረዳ ጫንያለው**

ተፈጥሮ ሳትሰስት ያለልክ በለገሰችው ድምፁ የተቹትን ሁሉ ሳይቀር በዙሪያው አሰባስቦ በሃሴት ያስጨፈረ የመድረክ ላይ ንጉስ እንደነበር ይነገርለታል። የሃገሪቱን ዘመናዊ ሙዚቃ በምርኩዙ ውስጥ ያዋለ ጀግናም እንደሆነ ምስክርነታቸውን ይሰጡለታል። ከሁሉም በላይ ግን ሀገር ወዳድነቱን በእንባ ጭምር የሚገልጽ መሆኑ ከሁሉም ሙዚቀኞች ለየት ያደርገዋል የሚባልለት ነው፡፡ የዛሬው የባለውለታዎቻችን አምድ እንግዳ ክቡር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሰሰ፡፡ እናም ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ያገኘናቸውን መጣጥፎች በማጠናቀር ውለታነቱ እንዴት ነበር ስንል ልናወጋችሁ ወደናል። መልካም ንባብ ፡፡



## ውልደትና እድገት

1933 ዓ.ም ዕለተ መስቀል ለአቶ ገሰሰ ቤተሰብ አውደ ዓመት ብቻ አልነበረም፡፡ ለጎጇቸው ሌላ የምስራች የተገኘበት ልዩ ቀን ነው፡፡ እማወራዋ ጌጤ ጉርሙ ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ የተገላገሉበት ልዩ ዕለት። መላው ቤተሰብ በዓሉን ድርብ አድርጎ ያሳለፈበት የስጦታ ጊዜ። በዚህ ቀን የተገኘው ፍሬ ለመላው ቤተሰብ የአዲሱ ዓመት ታላቅ በረከትም ነበር፡፡ በትዳር ለተጣመሩት ጥንዶች የዓይን ማረፊያ የሆነው ብላቴና የተገኘበት፡፡ ይህ ልጅ ደግሞ ጥላሁን ነው፡፡

ጥላሁን ተወልዶ ያደገው አዲስ አበባ ልዩ ስሙ ‹‹ጠመንጃ ያዥ›› በተባለ አካባቢ ሲሆን፤ እንደ እኩዮቹ ሆኖ አድጎበታል፡፡ ለሚያዩት ሁሉ ልጅነቱ የሚያጓጓ፣ መልኩ የሚያምር ፣ ቁመናው የሚማርክ ነበርም። ሆኖም በአዲስ አበባም ሆነ በሰፈሩ በአብሮነት እምብዛም አልዘለቀም፡፡ 14ኛ ዓመቱን ባከበረ ማግስት ከተማውን ለቆ ጉዞውን ወደ ወሊሶ አደረገ፡፡ ወሊሶ አያቱ ይኖራሉ፡፡ እናም እዚያ ለማደግ ነው ወደዚያ የተጓዘው፡፡

## ትምህርትና የሙዚቃ ጥሪ

ጥላሁንና ትምህርት የተገናኙት አዲስ አበባ በነበረበት ወቅት ሲሆን፤ የትምህርት ሀሁውን የጀመረውም በአካባቢው ከሚገኝ የራስ ጎበና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ በዚያ ፊደል እንዲቆጥር ተመዘገበ፡፡ ብዙም በቦታው ላይ ባለመቆየቱ የተነሳ ቀጣዩን ትምህርት የተማረው ወሊሶ ላይ ነው። በእርግጥ የእሱ ፍላጎት ከቀለሙ ጋር የሚገናኝ አልነበረም። ውስጡ ያደረው የሙዚቃ ፍቅር ይታገለዋል፣ ያሸንፈው ይዟል፡፡ ይህን ያስተዋሉት አያት ሁኔታውን አልወደዱም፡፡ ምክንያቱም የእርሳቸው ፍላጎት በትምህርቱ ብቻ ላይ እንዲያተኩር ነው፡፡

የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ ሱዳናዊው ሼድድ ግን ጥላሁንን በተለየ መልኩ አይተውታል፡፡ ፍላጎቱን አብዝተው ያከብሩለታል፡፡ ስለዚህም ፍላጎቱን እንዲሞላ ትኩረት ቸሩት፡፡ ችሎታውን መዝነውም ወደ ሱዳን ሄዶ ሙዚቃ እንዲያጠና ምክር ለገሱት። እርሱም ምክራቸውን ሰማና የተባለውን ባያደርግም ከራሱ ስሜት ጋር ሲታገል ቆየ፡፡ አንድ ቀን ግን ምክሩን እውን የሚያደርግበት እድል ገጠመው። ይህም የሀገር ፍቅር ቴአትር ባለሙያ የነበሩ ባለሙያዎች በትምህርት ቤታቸው የሙዚቃ ትዕይንት ለማሳየት የተገኙበት ነው፡፡ ከመጪዎቹ መካከል ደግሞ አቶ ኢዮኤል ዮሐንስ አንዱ ናቸው። እናም ጥላሁንም ቀረብ ብሎ ያለውን ችሎታና ፍላጎቱን አስረዳቸው፡፡ እዮኤል ጆሮ ሰጥተው አደመጡት፡፡ ፍላጎቱ ካለውም አዲስ አበባ መምጣት እንደሚችል ጠቆሙት፡፡ እንግዶቹ ከወሊሶ ከተሸኙ በኋላ ጥላሁን እንቅልፍ ይሉት አጣ። ትምህርቱን መማር፣ መከታተል ተሳነው፡፡

አንድ ማለዳ የጥላሁን ልብ ቆርጦ ተነሳ፡፡ ማንንም ሳያየው ከቤት ጠፍቶ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመረ። ሁኔታውን ያወቁት አያት ለዘመድ ነግረው ሰላይ ላኩበት፡፡ 15 ኪሎ ሜትር በእግሩ የተጓዘው ጥላሁን ቱሉ ቦሎ ሲደርስ አዳሩ ከአክስቱ ቤት ሆነ። ማግስቱን ጉዞ ከመቀጠሉ በፊት ግን ተይዞ ወደ ወሊሶ ተመለሰ፡፡

በአስገዳጅነት ተመልሶ ወሊሶ የገባው ጥላሁን በሆነበት ሁሉ አዘነ፡፡ እልህና ቁጭት ያዘው፡፡ በውስጡ ያደረውን የሙዚቃ ፍቅር ያደናቀፉበትን በሙሉ በክፉ ዓይን አያቸው፡፡

በቤቱ ከአንድ ቀን በላይ አልቆየም፡፡ በጭነት መኪና ተሳፍሮ ዳግም ጉዞ ጀመረ፡፡ አዲስ አበባ ያደረሰው እግሩ ከሀገር ፍቅር ቴአትር አገናኘው። የጥላሁን ምኞት ዕውን ሆነ፡፡ የውስጡ ፍላጎትና የሙዚቃው ፍቅር ገጠሙለት፡፡ የትናንትናው የወሊሶ ጉብል አዲስ አበባ ላይ ታዋቂ ለመሆን አልዘገየም። እንዳሻው የሚታዘዝለት ድንቅ ጉሮሮው የሰጡትን ግጥምና ዜማ እያንቆረቆረ በርካቶችን ይማርክ ያዘ። የዘመኑ ተወዳጅ ድምጻዊ በመሆን ቀዳሚም ሆነ፡፡

ጥቂት ጊዜያትን በሀገር ፍቅር የቆየው ጥላሁን ለሌላ ዕድል ታጨ፡፡ ወደ ክቡር ዘበኛ ተዛውሮ ከአንጋፋና ታዋቂ የሙዚቃ ሰዎች ጎን ተሰለፈ፡፡ የላቀ ዝነኝነቱን ተከትሎ ግን ፈተና አላጣውም፡፡ በታህሳሱ ግርግር ዘፍኖታል የተባለ ዜማ ትርጉም ተሰጥቶት ለእስር ዳረገው፡፡ ይህም ቢሆን መዝፈኑን አቁሞ አያውቅም። ይበልጡን ከእስር ከተፈታ በኋላ ጠነከረ። በዚህም ብዙዎች እርሱ ያልነካው የሕይወት ጫፍ፣ ያላነሰው የዓለም እውነታ የለም። ክፋትና ደግነት፣ ሀዘን ደስታ፣ ሕይወትና ሞት የለም ይሉታል፡፡

## የጥላሁን ሙዚቃና የሀገር ፍቅር

ጥላሁን ከሙያ አቻዎቹ የሚለየው በዘመናት ሂደት በተቻለው ሁሉ በሙዚቃ ሥራው ውስጥ ራሱን ከፍ እያደረገ መሄዱ ነው ይላሉ፡፡ ከአሁን በኋላ በቃው በሚባልበት ጊዜ በድንገት የሚያስደምም ሥራ ይዞ ብቅ ይላል፡፡ ‹‹ጥላሁን በላብ እየተጠመቀ መድረክ ላይ ወጥቶ ሲዘፍን በአካባቢው መድፍ እንኳ ቢተኮስ አይሰማም›› ሲሉ አስተያየታቸውን የሚሰጡም አሉ፡፡ ማለትም መመሰጥ ከምንም በላይ ይችላል። መመሰጥን ከሃገር ፍቅር አንፃር፤ ማስተማርን ከጀግንነት አኳያ እንዴት ሲያዋህደው እንደነበረ ጥቂቶቹን ግጥሞቹን በማንሳት እናውጋ፡፡

**አጥንቴም ይከስከስ ደሜም ይፍሰስላት፣**

አገሬን በጭራሽ አይደፍራትም ጠላት፡፡ የሚለው አንዱ ሲሆን፤ በ1967 ዓ.ም ኢትዮጵያ ባገጠማት ድርቅና ርሀብ የከፋ ችግር ላይ በወደቀችበት ዘመን ላይ ሆኖ መላው ዓለም ኢትዮጵያን ርዕስ አድርጎ ስለከፋው ርሀቧ፣ በየዕለቱ እንደ ቅጠል ስለሚረግፈው ምስኪን ህዝቧ በእጅጉ ሲያወራ ጥላሁን ግን የሙያ አጋሮቹን ሰብስቦ ከመደገፉ ባለፈ በእጁ የገባውን ግጥም ከዜማ አዋህዶ ለሁሉም ‹‹ይድረስልኝ›› ሲል በታላቅ ሀዘንና ለቅሶ

**ዋይ !ዋይ ሲሉ፣**  
**የርሀብን ጉንፋን ሲስሉ፡፡**  
**እያዘንኩ በዓይኔ አይቼ፣**  
**ምን ሳድርግ አለፍኳቸው ትቼ፡፡**  
**ወይ እማማ ወይ አባባ፣**  
**ብሰው ሲሉ ሆዴ ባባ፡፡**  
**አስጨነቀኝ ጭንቀታቸው፣**  
**ምንስ ሆኜ ምን ሳርጋቸው፡፡**  
**ሳያቸው አይኔ አፍጥጦ፣**  
**ተለየኝ ልቤ ደንግጦ፣**  
**ተብረከረከ ጉልበቴ፣**  
**ምን ሳድርግ ዋ! ድህነቴ€€**  
**በርሀብ ስቃይ ችነፈር፣**  
**ግማሹ ጎኔ ሲቸገር፡፡**  
**ክው ብሎ ደርቆ አፋቸው፣**  
**የእግዜር ውሀ ሲጠማቸው** እያለ አንጎራጎረ።

በዚህ ሙዚቃው ደግሞ ከሀገር አልፎ ባህር ማዶ ተሻገረ። ወገኖቹን ከችግር ታደገ፡፡ ምክንያቱም በእርሱ ጥበብ ለእርዳታ እጁን ብዙ ሰው ዘረጋ። ወገን ለወገኑ እንዲደርስ፣ አስከፊው የርሀብ ጊዜ እንዲታወስ አደረገ። ይህ አይረሴ ዜማ ዛሬ ድረስ ለመላው ኢትዮያውያን የክፉ ቀን ማስታወሻ እንደሆነ ዓመታትን ተሻግሯል።

ጥላሁን በዜማው ባለስልጣንን የሚቃወምና ድልንና ለውጥን ለሀገር የሚያሳይም ነው፡፡ በየትኛው ሙዚቃው ከተባለ ለአብነት ‹‹በአልማዝን ዓይቼ›› በዚህ ሙዚቃው በዘመነ ደርግ የነበረውን የስልጣን ሹምሽር በደንብ ተችቶታል፡፡ አድማጩን አንቅቶ የለውጥ አምጪ አድርጎበታል፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ ሶስቱን አልማዞች ከወቅቱ ሶስት የደርግ ባስልጣናት ጋር አመሳስሎ የራሱን ትርጓሜ ይሰጥ ነበርና ታሪክ እንደሚነግረን ደግሞ እነዚህ ሶስት ሰዎች የኢትዮጵያን የፖለቲካ ታሪክ የመቀየር ገጽታን ተላብሰው ነበር፡፡ እንዲህ መሆኑ ደግሞ ምርጫው ወደ ሌላ እንዲያደለና በመጨረሻ ጥሩወርቅ ከተባለችው ላይ እንዲያርፍ መገደዱን ጭምር ይነግረናል፡፡ ስለዚህም ጥላሁን የሀገር ለውጡ ላይ ሳይቀር ተሳትፎ ነበረው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

ሌላው ጥላሁንን ለየት የሚያደርገው በትግል ሜዳም አዋጊ ጀግና መሆኑ ነው፡፡ በተገኘባቸው የጦር አውድማዎች ጀግናን ማወደስ፣ ወታደሩን ማጀገን ያውቅበታል፡፡ በጦርነት መሀል ተገኝቶ ወደ ፊት በሉለት ይለይለትን አዚሟል፡፡ የጀግና ሰው ክብሩ ዳር ድንበሩ ሲል አነቃቅቷል፤ ዘማች ነኝን ዘፍኗል። ከሁሉም ግን የውትድርና ሕይወትን መሰረት አድርጎ ለጀግኖች ኢትዮጵያውያንና ቤተሰቦቻቸው መታሰቢያነት ያንጎራጎረው ይህ ዜማ ፍጹም አይረሴነትን እንደያዘ እስከዛሬ ቀጥሏል፡፡

**ስአገሬ ስታገል ስድንበሯ**  
**ከአገሬ ስታገል ስድንበሯ፣**  
**ተኝቻለሁ እኔ ከአፈሯ፡፡**  
**ስስድል ታሪኬን ስታወሱ፣**  
**ቤተሰቦቼን ግን እንዳትረሱ፡፡**  
**እንዳይራቡብኝ አስታውሱልኝ፣**  
**እንዳይራቆቱ አልብሱልኝ፡፡**  
**እንዳይቸገሩብኝ ልጆቼ፣**  
**አደራ ብያለሁ ወገኖቼ፡፡**

ጥላሁን ገሰሰና የሀገር ፍቅር ፈጽሞ አይነጣጠሉም። ስለሀገሩ ካሉት ደግሞ የዕንባው ነገር ይለያል፡፡ አገሩን እያነሳ አልቅሶ ታዳሚውን ጭምር ያስለቀሰባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው። ከጥላሁን የዕንባ ዜማዎች መካከል ስለነጻነት ያዜመው ስንኝ እንዲህ ይታወሳል፡፡

**እንኳንስ ደስታዬን -የሰውነቴን ሰው፣**  
**እንኳን ነጻነቴን- ጸጋ ክብሬን ትቼው፡፡**  
**በእናት ሀገር ምድር - በሚያውቀኝ፣**  
**በማውቀው ፣**  
**ስቃይ መከራየን ካንቺው ዘንድ ያድርገው፡፡**

ጥላሁን ገሰሰ በአማርኛ ከተጫወታቸው እጅግ በርካታ ዜማዎች በተጨማሪ በኦሮምኛና ሱዳንኛ ዘፈኖቹ ጭምር ይታወቃል፡፡ ሁሉም በሚባል መልኩም ዜማዎቹ ተወዳጅና ተደማጭ እንደሆኑም ምስክር የሚሆነው ዓመታትን መሻገራቸው ነው። ከዚህ አንጻርም የኢትዮጵያ የሙዚቃ ንጉስ ተብሎ ይጠራል፡፡

ጥላሁን በሕይወት ዘመኑ በርካታ ውጣውረዶችን አልፏል፡፡ በ1985 ዓ.ም በአንገቱ ላይ የደረሰበትን ጉዳት ጨምሮ በስኳር ህመሙ መነሻ ባጋጠመው ሕመም አንድ እግሩን አስከመቆረጥ ደርሷል። እንዲያም ሆኖ ከመድረክ የመለየት ፍላጎት አልነበረውም፡፡ ሁሌም ቢሆን ሙያውን ማሳየት፣ ለአድናቂዎቹም ፍቅሩን መግለጽ ይሻል፡፡

## የጥላሁን ሽልማቶች

ዕድሜውን ሙሉ ለሀገሩ ባበረከተው የኪነጥበብ ስራዎች ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት አግኝቷል፡፡ እንዲሁም ከኢትዮጵያ የኪነጥበብና የብዙኃን መገናኛ ሽልማት ድርጅት የሙሉ ዘመን ተሸላሚ ለመሆን ችሏል፡፡

## ጭስማው ፋሲካ

ጥላሁን ለግማሽ ምዕተ ዓመት በሙዚቃው ማማ ንጉስ ስለነበረው ክቡር ዶክተር ጥላሁን ገሰሰ ብዙ ማለት ይቻል ይሆናል፤ ነገር ግን መጨረስ አይቻልም፡፡ ገና በአፍላ የሙዚቃ ዘመኑ በሲራክ ታደሰ የተደረሰውን ‹ትንፋሼን› ስንሰማ ከሕይዎትም በላይ ሞትን ያልዘነጋ ንጉስ መሆኑን እንረዳለን። በሕይወት ካለፈ በኋላ በሀገር እንዲታወስና በሙያው እንዳይረሳ ያዜመ ብርቅዬ ዘፋኝ መሆኑንም እናረጋግጣለን፡፡ እስኪ ‹‹በትንፋሼን›› ምን አለ ካላችሁ በቃላት አዳምጡት፡፡

**ትንፋሼ ተቀርፃ ይቀመጥ ማልቀሻ፣**  
**ይህ ነው የሞትኩለት የእኔ ማስታወሻ፡፡**  
**ውበቷን ሳሞግስ -የለምለም ሀገሬን፣**  
**ማንም አይዘነጋው በጩኸት መኖሬን፡፡**  
**ዜማ እንጉርጉሮዬን የግሌን ቅላጼ፣**  
**ተቀርፃ ይቀመጥ ታሪኬ ነው ድምጼ፡፡**  
**ድምጻዊ ዘፋኝ ነኝ አንጎራጉራለሁ፣**  
**ይኸው ነው ታሪኬ ሌላ ምን አውቃለሁ፡፡**

ዕለተ ፋሲካ ለሁሉም ሰው ፍስሀ ሲሆን ለጥላሁን ቤተሰብ ግን ጨለማ ነበር፡፡ ሆኖም በማይረሱት ሙዚቃዎቹ ዘወትር ስለሚታሰብ ሀዘናቸውን ከሌሎች ጋር ተጋርተው ዕለቱን በደስታ እንዲያሳልፉ ይሆናሉ። እርሱ ሲታሰብም ከለቅሶ ይልቅ ሀሴትን ያደርጋሉ። ምክንያቱም እርሱ ከሚወዳት አገሩ፣ ከሚያከብረው መድረክና በፍቅር ከተንበረከከለት ሙያው በድንገት የተለየው ሚያዚያ 11 ቀን 2001 ዓ.ም በዕለተ ፋሲካ ሌሊት ቢለያቸውም ልደቱ በዕለተ መስቀል ተከብሮ በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ጎልቶ ይታያልና እርሱ አልሞተምን በየዓመቱ ያስባሉ። ልክ ነው ንጉስ በሀገሩ ሁሌ መከበሩ አይቀርምና አይሞትም፤ ሕያውነቱን በሥራዎቹ ይገልጣል፡፡

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ
ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency



ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# በጎዳና ላይ ቻምፒዮና የተሳተፈው የአትሌቲክስ ቡድን ተሸለመ

**ብርሃን ፈይሳ**

በውድድር ዓመቱ በሶስት ርቀቶች የዓለም ክብረወሰኖችን ሰብራለች፡፡ በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ሁለት የወርቅ ሜዳሊያዎችን በማጥለቅ እንዲሁም በዳይመንድ ሊጉ አሸናፊ በመሆን እጅግ ስኬታማ ዓመትን አሳልፋለች፡፡ ጠንካራዋ ኬንያዊት አትሌት ፌይዝ ኪፕዬጎን ዓመቱን ባለመሸነፍ ለማጠናቀቅም እቅድ ነበራት፤ ይሁን እንጂ ሃገሯን ወክላ በተሳተፈችበት የመጨረሻው ውድድር መረታቷ የግድ ሆኗል፡፡ አትሌቷን በመርታት የወቅቱ ተቀናቃኟ መሆኗን ያስመሰከረችው የመጪው ዘመን ኮከብ አትሌት ኢትዮጵያዊቷ ድርቤ ወልተጂ ናት፡፡

ወጣቷ አትሌት አዲስ በሆነችበት ርቀት በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና እንዲሁም ዳይመንድ ሊግ መድረኮች ኬንያዊቷን ተከትላት ከመግባት ባለፈ አሳማኝ በሆነ ብቃት ክብረወሰን በመስበርም ጭምር በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደው የዓለም የጎዳና ላይ ውድድሮች ቻምፒዮና በአንድ ማይል ፉክክር አሸናፊ ሆናለች፡፡ ወጣቷ ኢትዮጵያዊት ይህን ታሪካዊ ውጤት አስመዝግባ ወደ ሃገሯ ስትመለስም ‹‹ውድድሩ ካሰብኩት በላይ ነበር፤ ለሃገሬም ሆነ ለራሴ ይህንን ውጤት በማምጣቴ በጣም ደስተኛ ነኝ። ፌይዝ ኪፕዬጎን በጣም ጠንካራ አትሌት በመሆኗ እሷን ማሸነፍ በመቻሌ በጣም ደስተኛ ነኝ፡፡ ሁለት ጊዜ አብሬያት ሮጬ ሁለተኛ ደረጃን ይዤ ነበር ያጠናቀኩት፤ በዚህ ውድድር ላይም ስላሸነፍኳት ደስተኛ ነኝ፡፡ በቀጣይም ከዚህ የተሻለ በመስራት ለራሴና ለሃገሬ የሚያስደስትና ከዚህ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት



**በጎዳና ላይ ቻምፒዮና የተሳተፈው የአትሌቲክስ ቡድን ሽልማት ተበርክቶለታል፣**

አደርጋለሁ›› ብላለች፡፡

የመም አትሌት የሆነችው ድርቤ ለመጀመሪያ ጊዜ በጎዳና ውድድሮች ተሳትፋ ይህንን ውጤት ማምጣቷ አስደናቂ መሆኑን የሚናገረው ደግሞ አሰልጣኟ ኢሳ ሁሴን ነው፡፡ በዚህ ውድድር ላይ የተሳተፈችው ከዓለም ቻምፒዮናና ዳይመንድ ሊግ መልስ በተደረገ የጥቂት ቀናት ዝግጅት ነው፡፡ ይህ የአትሌቷ አቋም የሚያሳየውም የ1ሺ500 ሜትርን ክብረወሰን ጭምር ከኬንያዊቷ አትሌት መረከብ እንደምትችል ነው፡፡ ነገር ግን ጊዜ እና ስራ ይፈልጋል፤ በተከታታይ በተካሄዱ ውድድሮች ድርቤ የኪፕዬጎን ተፎካካሪ በመሆን ስነልቦናዋን መገንባት ችላለች፡፡ ጠንካራ ዝግጅት በማድረግም ለፓሪስ ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን ከመወከል ባለፈ አዲስ ክብረወሰንን ለማስመዝገብ አቅደው እየሰሩ መሆኑንም ጠቁሟል፡፡

በሺዎች የሚቆጠሩ አማተር ሯጮችን እንዲሁም የየሃገራቸውን ብሄራዊ ቡድን የወከሉ አትሌቶችን በማሳተፍ በላቲቪያ ሪጋ የተካሄደው የጎዳና ላይ የዓለም ቻምፒዮና በምስራቅ አፍሪካ አትሌቶች የበላይነት መጠናቀቁ የሚታወስ ነው፡፡ በዚህ ውድድር ተካፋይ የነበሩ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች 2የወርቅ፣ 4 የብር እና 1የነሃስ በጥቅሉ 7 ሜዳሊያዎችን በማስመዝገብ ከዓለምም ከአፍሪካም የሁለተኛነት ደረጃን ይዘዋል፡፡ ይህንን ተከትሎም ኢትዮጵያን የወከሉት አትሌቶች ትናንት ማለዳ ደማቅ አቀባበል ተደርጎላቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንም የወርቅ ሜዳሊያ ላጠለቁ 40ሺ ብር፣ ለብር ሜዳሊያ ባለቤቶች 30ሺ ብር፣ ለነሃስ ሜዳሊያ ተሸላሚዎች 15ሺ ብር እንዲሁም ዲፕሎማ ላመጡ አትሌቶች 10ሺ ብር በማበረታቻ መልክ አበርክቷል፡፡

ይህንንም ተከትሎ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደው በዚህ ውድድር ሜዳሊያ በማስመዝገብ፣ የዓለም ክብረወሰንን በመስበር እንዲሁም በቡዳፔስቱ የዓለም ቻምፒዮና በ1ሺ500ሜትር እና 5000ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ያገኘችውን ኬንያዊት አትሌት መርታት የተቻለበት በመሆኑ ልዩ እንደሚያደርገው ገልጻለች፡፡ ውድድሩ ከቡዳፔስት ማግስት የተካሄደ በመሆኑ እንጂ ምናልባትም የተሻለ ዝግጅት ተደርጎበት ቢሆን ከዚህ የተለየ ውጤት ሊገኝበት ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን የተገኘው ውጤት አስደሳች ሊባል የሚችል ነው፡፡ በዓለም አትሌቲክስ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በብሄራዊ ቡድን ደረጃ ከሚካሄዱ ውድድሮች ይህ ቻምፒዮና የመጨረሻው ሲሆን፤ በዚህም ኢትዮጵያ እንደ አጠቃላይ በአትሌቲክስ መልካም በሚባል ውጤት ዓመቱን እንደደመደመችም አክላለች፡፡

ከረጅም ጉዳት መልስ ወደ ውድድር የተመለሰው አትሌት ሃጎስ ገብረህይወት በ5ኪሎ ሜትር የወንዶች ውድድር የሃገሩን ልጅ አስከትሎ በመግባት የወርቅ ሜዳሊያውን የግሉ ሊያደርግ ችሏል፡፡ በቡዳፔስቱ የዓለም ቻምፒዮና ውጤት አለመምጣቱ የሚያስቆጨው አትሌቱ ህዝቡን ለመካስ ባደረገው ጥረት ውጤታማ ሊሆን እንደቻለ ይገልጻል። ከ3ዓመት ጉዳት በኋላ ወደ ውድድር ተመልሶ ውጤት ማስመዝገብ እንዲሁም የመጀመሪያው ቻምፒዮና እንደመሆኑ አስደሳች ነው፡፡ ውድድሩ ወደሚካሄድበት ሪጋ የነበረው ጉዞ እንዲሁም በውድድር ወቅት የነበረው ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ፈታኝ ቢሆንም ውጤት የመጣው ይህንን በመቋቋም ነው፡፡ ከጉዳት መልስ ውጤታማ ለመሆን በስነልቦናም ሆነ በአካል ብቃት ጠንካራ ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ይህ ውጤት ለቀጣዩ ኦሊምፒክ ሞራል ቢሆንም፤ አስቀድሞ ዝግጅት በማድረግ ውጤታማ ለመሆን አትሌቶች እየተቸገሩበት ያለው የማዘውተሪያ ችግር ሊቀረፍ እንደሚገባም አሳስቧል፡፡